# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 184 መጋቢት 4 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia





# "የኢትዮጵያ ተቋማት በአሕጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ተቋማት በአሕጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡

የኢትዮጵያ ተቋማት የስኬት ሽልማት መርሐ-ግብር በዓድዋ ሙዚየም ትናንትና ሲከናወን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለግብርና ሚኒስቴር /በስንዴ ልማት ፕሮግራም/፣ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ለኢትዮ ቴሌኮም፣ ለኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የዕውቅና ሽልማት አበርክተዋል፡፡

በወቅቱ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ተቋማት አቅማቸውን

"የኢትዮጵያ ተቋማት… ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መሠረተ ልማት ለማጠናቀቅ የፋይናንስ እጥረት ፈታኝ ሆኗል

**በሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

አዲስ አበባ፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች ያለውን የመሠረተ ልማት ግንባታ በወቅቱ ገንብቶ ለማጠናቀቅ የፋይናንስ እጥረት ፈታኝ ሆኗል ሲሉ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ስጦታው አካለ ገለጹ፡፡ ችግር ያለባቸው ቤቶችን በየሳይቱ ምን እንደጎደላቸው ተለይተው ችግሩን የመፍታት ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ኢንጂነር ስጦታው ከኢትዮጵያ ፕሬስ

የጋራ መኖሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የአንጋፋው ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ሥርዓተ-ቀብር ተፈጸመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አንጋፋው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ሥርዓተ- ቀብር በትናንትናው እለት ተፈጸመ፡፡

የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የጋዜጠኛው ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶች እንዲሁም የሙያ አጋሮች በተገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ አስኮ አካባቢ በሚገኘው አቡነ ሐብተማርያም ገዳም ተከናውኗል፡፡

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ከአባቱ ከአቶ ግደይ አምባዬና ከእናቱ ከወይዘሮ ሐረጉ ኃይትዖም መጋቢት 11 ቀን 1958 ዓ.ም.

የአንጋፋው ጋዜጠኛ… ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጎችን ያሳተፈ የማኅበረሰብ ውይይት ተካሂዷል

- መንግሥት ትጥቅ አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር ለመደራደር በሩ ክፍት ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ባለፉት ስድስት ወራት ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ በተለያዩ አካባቢዎች ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጎችን ያሳተፈ የማኅበረሰብ ውይይት መካሄዱን የሠላም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ መንግሥት ትጥቅ አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር ለመደራደር በሩ ምንጊዜም ክፍት መሆኑም ተገልጿል፡፡

የሠላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት በሁሉም ክልሎች ላይ ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጎችን ያሳተፈ የማኅበረሰብ ውይይት ተደርጓል፡፡

ዘላቂ ሠላምን… ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡- ገበዩ ገብሬ

አቶ ብናልፍ አንዱዓለም


AfriSky PLC
ETHIOPIA




0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY

ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory





# ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደርን በማስፈን ኢንቨስትመንትን ማበረታታት እንደሚገባ ተገለጸ

## - የባለሀብቶች የልማት መሬት አቅርቦት ላይ ያተኮረ የፖሊሲ ሰነድ ይፋ ሆኗል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደርን በማስፈን ኢንቨስትመንትንና የኢኮኖሚ ልማትን ማበረታታትና ግልጽና ወጥነት ያለው ፖሊሲ መዘርጋት እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኘው የአውሮፓ ቻምበር "የመሬት ተደራሽነት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ላሉ ባለሀብቶች የመሬት አሰጣጥ ሂደትን ማመቻቸት" በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ሰነድ ትላንት የግብርና ሚኒስቴርና የኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተገኙበት ይፋ ያደረገ ሲሆን፤ የፖሊሲ ሰነዱ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የኢንዱስትሪ ዞኖች ውጭ በልማት ሥራ ውስጥ የተሠማሩ ባለሀብቶች የልማት መሬት ከማግኘት ጋር ተያይዞ ስለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች እንደሚያትት ተገልጿል፡፡

የአውሮፓ ቻምበር በኢትዮጵያ አምባሳደር ተወካይ ዶክተር ዴቪድ ሪቫኔክ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደርን በማስፈን ኢንቨስትመንትንና የኢኮኖሚ ልማትን ማበረታታትና ግልጽና ወጥነት ያለው ፖሊሲ መዘርጋት ይገባል፡፡

የሰነዱ ዓላማ በኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት መሬት ከማግኘት ጋር በተያያዘ የግሉ ሴክተር የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በመለየት ለግሉ ሴክተር ዕድገት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ መሳብ ነው፡፡

ሰነዱ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ የቢሮክራሲያዊ መዘግየቶች፣ ቀድሞ የተዘጋጀ በቂ የኢንቨስትመንት መሬት አለመኖር፣ ከመጠን ያለፉ የካሣ ጥያቄዎች እና የካሣ አሰጣጥ አስተዳደር ችግሮች የሚያሳይ ነው፡፡

በክልላዊ መዋቅርና በመሬት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች ላይ በየጊዜው በሚደረጉ ለውጦች፣ የልማት መሬቶች ጋር ለመድረስ የመሠረተ ልማት አውታሮች ውስንነት፣ በፌዴራልና በክልል ባለሥልጣናት መካከል ያለው የቅንጅት ክፍተት፣ የማጭበርበር ተግባራት፣ የአስተዳደር አቅም ችግሮች እና የሃብት ውስንነቶች፣ የመሬት ድልድል ተመሳሳይ አለመሆን እና በባለሀብቶች መሬትን ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ምክንያት እንደሚባባሱ በሰነዱ ተመላክቷል፡፡

የፖሊሲ ሰነዱ በኢትዮጵያ መንግሥት ሊታሰብባቸው የሚገቡ የውሳኔ ሃሳቦችን ያስቀመጠ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ግልፅነትን፣ ፍትሐዊነትን እና ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደርን በማስፈን ኢንቨስትመንትን እና ኢኮኖሚ ልማትን የሚያበረታታ ግልፅና ወጥነት ያለው ፖሊሲ መዘርጋት አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

የመሬት አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን አቅም ማሳደግ፣ የፌዴራልና የክልል መንግሥት ቅንጅቶችን ማጎልበት፣ የፀረ-ሙስና ርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ግልጽነት ያለው የመሬት መዝገብ ማዘጋጀት በሰነዱ ከተነሱት ዋና ዋና ሃሳቦች መካከል ናቸው፡፡

ተጨማሪ ምክረ ሀሳቦች የካሣ ክፍያን ለማስላት መመሪያዎችን መፍጠር እና የመሬት ግምትን እንደ ግብርና ሚኒስቴር ካሉ አካላት ጋር ማስተባበር፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አገልግሎት ውጤታማነትን ማሻሻል፣ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች የመሬት ምደባ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ከተፈናቀሉ ግለሰቦች ጋር የምክክር ስብሰባዎችን ማካሄድ፣ በክልላዊ የመሬት አስተዳደር ቢሮዎች የመሬት አሰጣጥ ሂደቶችን ማቀላጠፍ እና እንደ ቬዬትናም ካሉ ሀገሮች የተሳካ የመሬት አስተዳደር ማሻሻያዎችን ተሞክሮ ማጥናትንም የሚያትት እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

የፖሊሲ ሰነዱ በኢንተርኔት አማካኝነት የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሲሆን፤ አንድ ለአንድ የተካሄዱ ቃለመጠይቆች እና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን፣ የንግድ ማኅበራትን፣ ባለሀብቶችን እና ምሑራንን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ የትኩረት ቡድን ውይይቶች ውጤቶችን ያካተተ መሆኑም ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ይገመግማል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ግብርና ሚኒስቴር ተወካዮች በመድረኩ እንደገለጹት፤ አብዛኛው የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ መንግሥት በቀጣይ በዘርፉ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች አጋዥ ሲሆን፤ ሰነዱን ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ጥናቶች ተደርገው በትብብር መሥራትን ይጠይቃል፡፡

# በኢትዮጵያና በማልታ መካከል የንግድና የኢንቨስትመንት ልውውጥን ለማሳደግ እየተሠራ ነው

## - የመጀመሪያው የኢትዮጵያና ማልታ ቢዝነስ ፎረም ተካሂዷል

**ሞገስ ፀጋዬ**



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያና በማልታ መካከል የንግድና የኢንቨስትመንት ልውውጥን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ አስታወቁ፡፡

በፎረሙ ላይ ከማልታ በተለያዩ ዘርፎች የተሠማሩ ባለሀብቶችና የተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ በፎረሙ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ የፎረሙ መካሄድ ኢትዮጵያና ማልታ በንግድና በኢንቨስትመንት ያላቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር መሠረት ይጥላል፡፡

የኢትዮጵያና የማልታ ግንኙነት እያደገ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህም በተግባር የተደገፈ ትብብር ስለመኖሩ ማሳያ ነው፡፡ በሁለቱ ሀገራት መካከል ጠንካራ የንግድና ኢንቨስትመንት ልውውጥ እንዲኖር እየተሠራ ነውም ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ በማደግ ላይ ያለ ኢኮኖሚ ባለቤት ናት፡፡ እንዲሁም ወደ አፍሪካ ገበያ ለመግባት እንደ በር ታገለግላለች፡፡ ይህም ለዓለም አቀፍ ባለሀብቶች ትልቅ ዕድል ነው፡፡

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የንግድ ቀጣና አባል መሆኗ ለአልሚዎች ተጨማሪ እድል ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በኢትዮጵያ በተለዩና ቅድሚያ በሚሰጣቸው በግብርና፣ በአምራች ዘርፍ፣ በቱሪዝምና በአይሲቲ ዘርፎች የማልታ ባለሀብቶች ቢሳተፉ አዋጭ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ኢትዮጵያና ማልታ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አላቸው ያሉት አምባሳደሩ፤ ለሁለቱ ሀገራት ሁለንተናዊ ትብብር እ.ኤ.አ በ2021 የማልታ መንግሥት በአዲስ አበባ ኤምባሲውን ከፍቶ አስፈላጊ ክንውኖች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

አምባሳደር ምስጋኑ፤ በተለያዩ ጊዜ በሁለቱ ሀገራት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተደረጉ ጉብኝቶች የሁለትዮሽ ግንኙነቱ በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አስችሎታል ብለው፤ በአቪዬሽን፣ በሳይበር ደህንነትና በቱሪዝም ረገድ በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ መደረሱንም ጠቅሰዋል፡፡ ወደፊት መሰል ስምምነቶች እንደሚኖሩ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያና የማልታ የቢዝነስ ፎረም ትብብር የሁለቱን ሀገራት ሀብት ለእድገት ለመጠቀም ይረዳል ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ከማልታ ጋር ያላትን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማጠናከር ጠንካራ ፍላጎት አላት፡፡ በቢዝነስና በንግድ ዘርፍ ያለው ትብብር በሚፈለገው ልክ ያላደገ በመሆኑ ወደፊት ጠንካራ የንግድ ትብብር እንዲኖር ይሠራል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የማልታ አምባሳደር ሮናልድ ሚካልፍ በበኩላቸው፤ ማልታ እ.ኤ.አ በ2021 በኢትዮጵያ ኤምባሲዋን ከፍታ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማጠናከር እየሠራች ነው ብለዋል፡፡

እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጋር በተለያዩ ዘርፎች በትብብርን ሊያጠናክሩ በሚችሉ ዘርፎች እየሠራች ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በኢትዮጵያ በርካታ እድሎች መኖራቸውን በመግለጽ፤ እድሎችን ለመጠቀም አስፈላጊውን ሁሉ ሥራ እንደምሠራ ገልጸዋል፡፡

ፎረሙ በሁለቱ ሀገራት መካከል ጠንካራ የንግድና የኢንቨስትመንት ትስስር ለመፍጠር ያግዛል ያሉት አምባሳደሩ፤ በየጊዜው የንግድና ኢንቨስትመንት ልውውጦች እያደጉ መጥተዋል፡፡ ማልታ ለኢትዮጵያ ወደ አውሮፓ ገበያ ለመግባት ጠቃሚ መሆኗን በመግለጽ፤ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ከንግድ ባሻገር በሁሉም ዘርፍ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

# በተግባርና በምርምር የተደገፈ የጤና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ፕሮግራም ይፋ ሆነ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በተግባርና በምርምር የተደገፈ የኅብረተሰብ ጤና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ፕሮግራም ጤና ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባና ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ይፋ አደረጉ።

በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን "ዶክተር ኦፍ ፐብሊክ ኸልዝ ፕሮግራም" ወደ ተግባር ለማስገባት ትናንት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተካሂዷል።

በጤና ሚኒስቴር የሰው ሀብት ልማት ማሻሻያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አሰግድ ሳሙኤል በውይይቱ ወቅት ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን "ዶክተር ኦፍ ፐብሊክ ኸልዝ ፕሮግራም" ወደ ተግባር ለማስገባት እየተሠራ ነው።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በጤናው ዘርፍ ያሉ አመራሮች ብቃታቸውን የሚያሳድጉበትና የጤናውን ሥርዓት የሚመሩበት የተሻለ እውቀት እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

ፕሮግራሙ በአዲስ አበባ እና ሐረማያ ዩኒቨርስቲዎች ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራው ተጠናቋል ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ የጤናው ዘርፍ አመራሮች በተግባር የተደገፈና በምርምር የታገዘ የኅብረተሰብ ጤና ላይ እንዲሠሩ እገዛ እንደሚያደርግ አመላከተዋል።

ሠልጣኞቹን የሲቪል ሰርቪስ ሕግን በተከተለ መልኩ የመመልመልና የማወዳደር እንዲሁም በአተገባበሩ ላይ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራን ሚኒስቴር መሥሪያ



ቤቱ የሚሠራ ሲሆን፤ ሥልጠናውን በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ለመጀመር ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የሐረማያ ዩኒቨርስቲ የጤናና ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር አሕመድ መሐመድ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዶክተር ኦፍ ፐብሊክ ኸልዝ ፕሮግራም በኅብረተሰብ ጤና ዘርፍ የሚሠሩ ምሩቃንን ለማፍራት ያለመ የትምህርት መስክ ነው።

የፕሮግራሙ ዓላማ የማኅበረሰቡን የጤና ችግር በመለየት የመፍትሔ ሀሳቦችንና አዳዲስ እውቀቶችን በማፍለቅ የኅብረተሰብ ጤና ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ምሩቃንን ማፍራት መሆኑን አስታውቀዋል።

ዩኒቨርስቲው ፕሮግራሙን ለመጀመር የተለያዩ ምርምሮችን በማድረግ የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለማስረዳትና ፕሮግራሙን ለማስተግበር የሚያስፈልገውን የትምህርት ካሪኩለም ለመቅረጽ ከአምስት ዓመት በላይ ጊዜ መውሰዱን ገልጸዋል።

ፕሮግራሙን ለመተግበርና ለማስፈጸም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማጥናትና በማዘጋጀት ከጤና ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

ሠልጣኞቹ የተለያዩ የጤና አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ በመዘዋወር የማኅበረሰቡን ችግር በመለየት የመፍትሔ ሀሳቦችን በማመንጨት ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆኑ ከሌሎች የትምህርት መስኮች ልዩ ያደርገዋል ብለዋል።

የዩኒቨርስቲው ትምህርቱን ለመጀመር የሚያስችለውን ሙሉ ዝግጅት ማጠናቀቁን ገልጸው፤ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ እነማን ናቸው የሚገቡት፣ በምን መስፈርት ነው የሚለውን የጤና ሚኒስቴር መልምሎ ሲያቀርብልን እንጀምራለን ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ ኮንትኔታል የጤና አጠባበቅ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የማነ ብርሀን (ፐ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዶክተር ኦፍ ፐብሊክ ኸልዝ ፕሮግራም በጤና ሥርዓቱ ላይ ፕሮግራሞችን በማቀድ፣ በማስፈጸምና በመገምገም የሚያገለግሉ ከፍተኛ ምሑራንን ለማፍራት ያለመ ነው።

ፕሮግራሙ በሀገሪቱ ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር የሚመጣጠን የጤና ባሕል ለመገንባት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልጸው፤ ለፕሮግራሙ ስኬታማነት ጤና ሚኒስቴር ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

ለፕሮግራሙ ስኬታማነት ቴክኒካል ድጋፍ የሚያደርግ 10 አባላት ያለው የቴክኒካል አማካሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል።

ዜና

# ምክር ቤቱ በትናንቱ ስብሰባው፡-
## - የሕዝባዊ በዓላት አከባበርን የተመለከተ ረቂቅ አዋጅ ለቋሚ ኮሚቴ መርቷል
## - የ16 ዳኞችን ሹመት አጽድቋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ሕዝባዊ በዓላትን በመወሰን፣ ሕጋዊ እውቅና በመስጠትና ለሕዝባዊ በዓላት አከባበር አስፈላጊውን ጥበቃና የሚዲያ ሽፋን ከመንግሥት እንዲያገኙ በማድረግ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ማሳደግ እንደሚገባ ተገለጸ፡፡የ16 ዳኞች ሹመትም ፀድቋል፡፡



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 16ኛ መደበኛ ስብሰባው የሕዝብ በዓላትን፣ እና የበዓላት አከባበር ለመወሰን የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብን አጽድቋል።

የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትሩ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ የአዋጁን አስፈላጊነት ሕዝባዊ በዓላት ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ታሪካዊ እና ማኅበረሰባዊ ሥርዓታቸውን በጠበቀ ሁኔታ በሠላምና በድምቀት እንዲከበሩ በማድረግ ያላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ማድረግ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

የሕዝብ በዓላት ለዜጎች ሥነ ምግባርና ሥነ ልቦና ግንባታ፣ ለሀገርና ለሕዝብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ በመሆኑ ሕጋዊ እውቅና መስጠትና በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበሩ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አቶ ተስፋዬ አንስተዋል፡፡

የሕዝብ በዓላት አስፈላጊው የመንግሥት ጥበቃ እና ትኩረት ተሰጥቷቸው ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊና ታሪካዊ ሥርዓታቸውን ጠብቀው በድምቀት፣ በሠላም እና የዜጎችን የእርስ በእርስ መልካም ግንኙነትና መተሳሰብ በሚያጎለብት መንገድ እንዲከበሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

የሀገርና የሕዝብን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያጎለብት ሁኔታ እንዲከበሩ ለማድረግ አዲስ ሕግ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን አመልክተዋል፡፡

ምክር ቤቱ የ16 ዳኞች ሹመትንም አጽድቋል፡ ፡ከተሿሚዎቹ መካከል ሦስቱ ሴቶች ናቸው፡፡ ተሿሚዎቹ በፍትሕ ሥርዓቱ የተጀመረውን ሪፎርም ለመተግበር እንደሚያግዙ ተስፋ ተጥሎባቸዋል ብለዋል።

በፍርድ ቤት የመዝገብ መደራረቦች መታየታቸውን በማስታወስም፤ የሚታዩ የሥራ ጫናዎችን እንደሚያቃልሉም ይጠበቃል ብለዋል፡ ፡ፍትሕን ለማስፈን ተሿሚዎቹ በቂ የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅትና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው መሆናቸውን የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ተናግረዋል።

የተለያዩ ሂደቶችን አልፎ ለሹመት መብቃታቸውን በመጠቆምም፣ ሂደቱ በቀጣይ ብዝኃነትን ባማከለ መልኩ እንዲተገበር ይደረጋል፣ ስብጥሩ ኢትዮጵያን እንዲመስል ይደረጋል፣ ለተግባሩ ተጨማሪ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች የተመራው ሌላው የኢትዮጵያ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ በሀገሪቱ ብሎም በአፍሪካ፣ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዘርፎች ለሀገርና ሕዝብ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሰው ልጆች የሚጠቅም የላቀ ተግባር



**አቶ ተስፋዬ በልጅጌ**

የፈጸሙ ሰዎችን ወይም አካላትን እውቅና በመስጠት ሌሎች አርዓያቸውን እንዲከተሉ ለማድረግ መሆኑን አቶ ተስፋዬ ጠቁመዋል፡፡


በሕገ መንግሥቱ መሠረት ማስፈጸሚያ አዋጅ ሳይወጣላቸው እየተሰጡ ያሉ የተለያዩ ሽልማቶችን ወጥ የሆነ ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖረው ለማስቻል መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

# ለሴቶች ተጠቃሚነት የመንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ትብብር ወሳኝ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶችን ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ በመንግሥታትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል የሚደረገው የጋራ ትብብር ወሳኝ መሆኑን በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ ገለጹ፡፡

የጃፓኑ ኢቶቹ ኮርፖሬሽን እና ዩኤንፈፒኤ ኢትዮጵያ በወር አበባ ጤናና ንፅሕና አጠባበቅ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኑሮ በማሻሻል ተጠቃሚ ለማድረግ ያለመ ስምምነት አድርገዋል።



በስምምነቱ ላይ በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ እንደገለጹት፤ ስምምነቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የግል ኩባንያዎች እንዲሁም ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የሴቶችን ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ ያግዛል፡፡

"ለጃፓን መንግሥት የሴቶችን ተጠቃሚነት ማጎልበት የልማት ትብብራችንን ከሚመሩት ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው" ያሉት አምባሳደር ሺባታ የጃፓን መንግሥት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የመከላከልና የፆታ እኩልነትን የማስፈን ተግባሩን ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዚህም የጃፓን መንግሥት በዩኤንፈፒኤ ኢትዮጵያ በኩል በአማራና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለሚገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች ድጋፍ እንደሚያደርግ አንስተው፤ ሴቶችን ለማብቃት የራሳቸውን ገቢ ማግኘት የሚችሉበትን እድል መፍጠር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የድጋፍ ስምምነቱ ሴቶችና ልጃገረዶች ያላቸውን አቅም አውጥተው እንዲጠቀሙ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ነው ያሉት ደግሞ በኢትዮጵያ የዩኤንፈፒኤ ተወካይ ኮፊ ኮአሜ ናቸው፡፡

ይህ ስምምነት የሴቶችንና የልጃገረዶችን ሕይወት ለመለወጥ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግና ዳግም ጥቅም ላይ የሚውሉ የንፅሕና መጠበቂያዎችን ለማምረት እንደሚያግዝ አመላክተው፤ ዩኤንፈፒኤ የማኅበራዊ ልማት ግቡን ለማሳካት የሚያደርገውን ጥረት እንደሚያግዝ ገልጸዋል፡፡

የወር አበባ ጤናን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሀብቶች በቂ አለመሆን ሴቶችና ልጃገረዶች በትምህርት፣ በማኅበረሰብ ተሳትፎና የኑሮ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳይሳተፉ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የኢቶቹ ኮርፖሬሽን ጀነራል ማናጀር አኪኮ ሽኖዳ በበኩላቸው፤ የኢቶቹ ኮርፖሬሽን በጃፓን ከሚገኙ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች አንዱ መሆኑንና በኢትዮጵያ እ.አ.አ በ1960 ሥራ እንጀመረ አንስተው፤ ተቋሙ በቴክስታይል፣ በማኑፋክቸሪንግና በብራንድንግ ቢዝነስ ውስጥ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የኢቶቹ ኮርፖሬሽን ከዩኤንፈፒኤ ጋር በመሆን ዳግም ጥቅም ላይ የሚውልና ፈሳሽን መምጠጥ የሚችል የሴቶች ንጽሕና መጠበቂያ እንዴት ማምረት እንሚቻል የእውቀትና የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸው፤ የኢቶቹ ኮርፖሬሽን ለኢትዮጵያውያን ዜጎች የተለያዩ ክህሎቶችን እንደሚያስተምርና የሥራ እድል እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

# በአካባቢ ጥበቃ
## ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ብቻ የሚያስተናግዱ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአካባቢ ጥበቃ ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ወንጀሎችን ለመከላከል የአካባቢ የወንጀል ችሎት ብቻ የሚስተናግድባቸው ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለማፅደቅ እየተሠራ ነው ሲል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሕግና ደረጃዎች ዴስክ ኃላፊ ተወካይ የሆኑት አቶ መስፍን ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአካባቢ ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ወንጀሎችን ለመከላከልና በአካባቢ ወንጀል መከላከል ዙሪያ የተደነገጉ የሕግ ማቀፎችን በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ ለማድረግ የአካባቢ ጉዳዮችን ብቻ የሚያስተናግዱ ፍርድ ቤቶች መቋቋም አለባቸው፡፡

ፍርድ ቤቶችን ከሚያስፈልጋቸው የሰው ኃይል ጋር ለማቋቋምና የአካባቢ ወንጀልን የሚከላከሉ የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎችን በሚፈለገው ሕግ ተፈፃሚ ለማድረግ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለማፀደቅ እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የአካባቢ ብክለትን፣ የኬሚካል አያያዝን፤ የድምፅ ማጉያ አጠቃቀምን በአጠቃላይ የአካባቢ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የሕግ ማቀፎችና ድንጋጌዎች ቢኖሩም አሁን አካባቢ ላይ እየደረሰ ካለው ወንጀል አንፃር በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ እየሆኑ አይደለም ብለዋል፡፡

የአካባቢ ወንጀልን ለመከላከል የተደነገጉ የሕግ ማቀፎችን በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ ለማድረግና ተጠያቂነትን ለማስፈን የአካባቢ ወንጀል ችሎት ለብቻ የሚስተናገዱባቸው ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለማፅደቅና ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አሁን ባለው የፍርድ ቤት አሠራር የአካባቢ ጉዳዮችን ብቻ የሚያስተናግዱ ችሎቶች የሉም ያሉት አቶ መስፍን የአካባቢ ጉዳዮች ችሎት ለብቻ በፍርድ ቤት እንዲታዩ አደረጃጀት የሚሠራ ረቅቅ አዋጅ ለማፅደቅ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ የአካባቢ ወንጀሎች የሚዳኙበትን ችሎት አደረጃጀት ሁኔታን የሚያሳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ፍሰት ባለው መልኩ የአካባቢ የወንጀል ተጠያቂነት ሥራ የተቀላጠፈ እንዲሆን ያደርጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በተለያዩ አዋጆች ተደንግገው የሚገኙት የአካባቢ ወንጀል መከላከል አዋጆችና ደንቦችን፣ የቅጣት ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት ለመፍጠር የሚያስችል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ፍርድ ቤቶች፣ ዐቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች ስለአካባቢ ወንጀል ግንዛቤው ኖሯቸው እንደሌሎች ወንጀሎች ክስ እንዲመሠርቱ የሚያስችልም ነው ብለዋል፡፡

በአካባቢ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ማለትም ብክለትን፤ ቆሻሻ መጣል፤ የድምፅ ማጉያን፤ ለግንባታ ግብዓት በመውሰድ የመሬት አቀማመጥ ተፈጥሮን የሚያሳጡ ወንጀሎችን ለመከላከልና ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት ረቂቅ አዋጁ ትልቅ ሚና አለው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# በጉጂ ዞን 60 ሺ ሄክታር የበጋ ስንዴ እየለማ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ጉጂ፡- በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን በበጋው የስንዴ ልማት 60ሺ ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ የማልማት ሥራ መጀመሩንና እቅዱን ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ዞኑ አስታወቀ፡፡ በ2015 ዓ.ም ከነበረው ምርት አምስት እጥፍ በላይ ለማሳደግም እየተሠራ ነው ተብሏል፡፡

የጉጂ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ነጋሽ ቡላላ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በበጋው የመስኖ ስንዴ ልማት በሰፊው የሚተገበር መሆኑንና ለዚህም የተለየ የእርሻ ቦታ እና እምቅ አቅም መኖሩን ጠቁመዋል፡፡ በተለይም የአካባቢ አየር ፀባይ ምቹነትና የተደረገው ቅድመ ዝግጅት ከታቀደው በላይ ለማልማት የሚያስችል መሆኑንም አስገንዝበዋል፡፡

በተካሄዱ ጥናቶች እስከ 100ሺ ሄክታር ድረስ የበጋ ስንዴ ማልማት የሚያስችል አቅም መኖሩ ተለይቷል ያሉት አቶ ነጋሽ፤ ዞኑ ካለው ሰፊ የእርሻ መሬት ተጨማሪ ተስማሚ የአየር ፀባይ አለ፤ ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ የውሃ ሃብት በመኖሩ ለመስኖ ሥራው ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

እንደ ዞኑ አስተዳዳሪ ከሆነ፤ 2014 ዓ.ም በዞኑ በነበረው የበጋ የመስኖ ስንዴ ልማት አምስት ሺህ ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ማድረግ ተችሏል፡፡

ይህንንም መነሻ በማድረግና ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2015 ዓ.ም ከአምስት ሺህ ሄክታር ወደ 11ሺ ሄክታር የማሳደግ ሥራ የተከናወነ ሲሆን ይህንንም አቅድ ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ተችሏል ብለዋል፡፡

ይሁንና ዞኑ ካለው የተፈጥሮ ሃብት፣ የአመራር ዝግጁነት፣ የባለሙያዎች ጥረት፣ የፌደራሉ እና የክልል መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል አኳያ ይህም አነስተኛ መሆኑን መገንዘብ በመቻሉ በ2016 ዓ.ም ይህን አኃዝ በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል፡፡

በዚህም መሠረት በ2016 ዓ.ም 42 ሺህ ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ወደ ሥራ የተገባ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ነጋሽ፤ በአሁኑ ወቅት በተካሄደው ግምገማ እና የእቅድ ክለሳ ከሚታሰበው በላይ እጅግ በላቀ ሁኔታ መሥራትና ማሳካት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ከ42 ሺህ ሄክታር ወደ 60 ሺህ ሄክታር የማሳደግ ሥራ መከናወኑንና ዞኑ ቀደም ሲል በበጋ የመስኖ ስንዴ ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረ ሲሆን ይህን ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት በመሰጠቱ በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱንም ዋና አስተዳዳሪው አስረድተዋል፡፡

የጉጂ ዞን፤ 13 ወረዳዎችን ያቀፈ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ዞኖች ከፍተኛ የስንዴ ምርት፣ ደን ልማት እና የእንስሳት እርባታ፣ ማዕድን ሃብት፣ የቱሪዝም እና ሌሎች ሃብቶችን የያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡

# ዘላቂ ሠላምን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ የማኅበረሰብ ውይይት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ብናልፍ ባለፉት ስድስት ወራት በሁሉም ክልሎች ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጎችን ያሳተፈ የማኅበረሰብ ውይይት ተደርጓል ብለዋል፡፡

ከኅብረተሰቡ ጋር ችግሮች ወደ ግጭት፣ ብጥብጥና ጥፋት ሳይሸጋገር እንዲቆም የሚያስችሉ ውይይት መካሄዱን ጠቅሰው ከሃይማኖት መሪዎች፣ መምሕራንና ምሑራን ጋር በሠላም ዙሪያ ጠንካራ ውይይቶች እንደተካሄዱ ገልጸዋል፡፡

የዘላቂ ሠላም ግንባታ ሥራ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሠላም ክበባት ተቋቁመው ወደ ሥራ መግባታቸውን በመግለጽ ተማሪዎች ልዩነቶችን በሠላማዊና በሠለጠነ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ እንደሚፈጥር ጠቁመዋል፡፡

ቀደም ባሉ ዓመታት ትምህርት ቤቶች ሁከት የሚካሄድባቸው የግጭት መቀስቀሻ ሲደረጉ ቆይተዋል ያሉት አቶ ብናልፍ በትምህርት ተቋማት ሠላማዊ የመማር ማስተማር ተግባር እንዲኖር ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

በሀገር ግንባታ ላይ የልሂቃን ተፅዕኖ ትልቅ በመሆኑ በርካታ ውይይቶች መደረጋቸውን ጠቅሰው የምሑራን በሀገር ግንባታ ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያግዝ የንቅናቄ መድረኮች መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡

ወጣቶች ከክልላቸው ውጪ በመሄድ የሕይወት ተሞክሮ እንዲወስዱና በሀገር ግንባታው ላይ የአብሮነት እሳቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ በመግለጽ በወጣቶች በጎ ፈቃድ አገልግሎት እስካሁን 50 ሺህ ወጣቶች ተሳታፊ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በፌዴራሊዝም ግንባታ የክልሎችን ግንኙነት ጠንካራ ለማድረግ አመራሮች የሚሳተፉበት ፎረሞች መቋቋማቸውን ጠቅሰው እውነተኛ ፌዴራሊዝም ሥርዓት በመገንባት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በግጭት መከላከል የቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ሥርዓት የዘመነ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው ችግሮች በሠላም ሁኔታ መተንተኛ ማዕከላት ተተንትነው ግብረ መልስ እየተሰጠ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

የሀገርን ሠላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ቁልፉ ነገር ውይይትና ንግግር ነው ያሉት አቶ ብናልፍ መንግሥት ዛሬም ችግሮችን እንነጋገርና እንፍታ የሚል አቋም አለው ብለዋል፡፡

መንግሥት ትጥቅ አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር ለመደራደር ዝግጁ መሆኑን ጠቅሰው የኢትዮጵያ ችግር ከውይይትና ንግግር ያለፈ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

በግጭትና ጦርነት ምክንያት በዜጎች ሕይወት፣ ኢኮኖሚያዊና የአብሮነት እንቅስቃሴ ላይ ችግር እያደረሰ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ በኃይል የሚደረግ መገዳደል ሀገሪቱን ወደ ኋላ ይመልሳል እንጂ ወደ ፊት የማራመድ ዕድል የለውም ብለዋል፡፡

በሀገራዊ ምክክሩና ሌሎች መድረኮችንም በመፍጠር ችግሮችን በሠለጠነ መንገድ ተወያይቶ መፍታት አዋጭ መሆኑን ጠቅሰው መንግሥት ያቀረበውን የሠላም ጥሪ ተቀብሎ በውይይትና በንግግር ችግሮችን ለመፍታት ለሚመጣ የትኛውም አካል በሩ ክፍት መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

# “የኢትዮጵያ ተቋማት በአሕጉርና ዓለም....

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በማጠናከር በአፍሪካና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያሳድጉበትን መንገድ መፍጠር እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ተቋማት የስኬት ሽልማት ሲዘጋጅ ጥቂት ተቋማትን አርዓያ አድርጎ በመውሰድና ዕውቅና በመስጠት በርካታ ድርጅቶች የስኬት ፈለጉን እንዲከተሉ በማሰብ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከተሸላሚዎች መካከል የሆነው የግብርና ሚኒስቴር በስንዴ ልማቱ ከአፍሪካ አንደኛ ከመሆን አልፎ ተወዳዳሪዎቹን ማጠናከር እንደሚገባው ገልጸዋል።

ሽልማቱ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ልፋትና ውጤት የተሰጠ ዕውቅና መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባም ተናግረው፤ ተቋሙ አሁን ላይ በስንዴ ልማት ያስመዘገበውን ስኬት በሌሎች ምርቶችም በመድገም በአሕጉር ደረጃ ያለውን አቅም ማሳደግ እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተጨማሪ የኢትዮጵያ አየር መንገድም በአፍሪካ ቀዳሚ ብቻ ሳይሆን በዓለምም ተወዳዳሪ መሆኑን ከግምት በማስገባት ተሸላሚ መሆኑን አንስተው፤ ተቋሙ በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ያሳየውን ብልሃትና ጥንካሬ በማስቀጠል የተሻለ ስኬት ማስመዝገብ እንደሚገባው አመላክተዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም በበኩሉ ከ75 ሚሊዮን በላይ ተጠቃሚዎችንና በቴሌብር አማካኝነት 43 ሚሊዮን ደንበኞችን ማፍራቱን አንስተው፤ ይህ ሥራው የአንዳንድ አፍሪካ ሀገራትን ሙሉ ሕዝብ መሸፈን የሚችል መሆኑን መዘንጋት እንደማይገባ አውስተዋል።

ተቋሙ በግብር ክፍያም ሆነ በቴክኖሎጂ የኢትዮጵያን ዕድገት እያረጋገጠ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ 120 ሚሊዮን ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ በመንቀሳቀስ እንዲሁም በአፍሪካ ደረጃም ተጨማሪ ሥራዎችን በማከናወን ስኬታማነቱን ማሳደግ እንደሚገባው አሳስበዋል።

ከተሸላሚዎች መካከል የሆነው የኢትዮጵያ ፖስታም ከኪሳራ ወጥቶ ትርፋማና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተወዳዳሪ መሆኑን አድንቀው፤ የተጀመረው የለውጥ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

ተቋሙ በወጣት አመራሮቹ በመታገዝ ሌብነትን በመከላከልና ዘመናዊ አሠራሮችን በማስቀጠል የጀመረውን ስኬት ማስፋፋት እንደሚገባው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

ሌላኛው የስኬት ተሸላሚ የሆነው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት በተመሳሳይ ወደ ውድቀት እያመራ የነበረ መሆኑን አስታውሰው፤ ከለውጡ በኋላ በፕሮጀክቱ አመራሮችና በሠራተኞቹና በፀጥታ ኃይሎች አማካኝነት ግንባታው በጥራትና በፍጥነት እንዲከናወን መደረጉን አንስተዋል።

ግንባታውን ለማስቆም የተለያዩ ማታለያዎችና ሴራዎች ቢፈጸሙም ሁሉንም ፈተናዎች አልፎ መደማጠናቀቂያው መድረሱን አስታውቀው፤ የኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት ያሳየና በቀጣይም በአፍሪካ ደረጃ ለሚገነቡ ግድቦች የልምድ ማዕከል ሆኖ ማገልገል እንዳለበት አመላክተዋል።

አምስቱም ተቋማት ሽልማቱ የተበረከተላቸው በዋናነት ከለውጡ ወዲህ ባስመዘገቡት ሪፎርም ብቻ ሳይሆን በአሕጉር ደረጃ ባላቸው ስኬት መሠረት ነው፤ ይህን ስኬታቸውን ቀጣይነት እንዲኖረው ማስቻል ይኖርባቸዋል ብለዋል ።

በአሕጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ መወዳደር የሚችሉ የተለያዩ ተቋማት አሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተቋማቱን በመለየትና በማጠናከር መላው ኅብረተሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

የተሸላሚ ተቋማትና የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ የዕውቅና ሽልማቱን የተቀበሉ ሲሆን፤ የስኬት ሽልማት መርሐ-ግብሩ ቀጣይነት እንደሚኖረው ተገልጿል።

# የአንጋፋው ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ሥርዓተ-ቀብር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሱዳን ሀገር ከሰላ ግዛት ተወለደ።

ጋዜጠኛ እዮብ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱ በሱዳን ከሰላ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከታተለ ሲሆን፤ ከዚያም የከፍተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በቲዩኒያን ከሰላ ቦይስ ማርች ተከታትሏል፡፡

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕንጻ ኮሌጅ ገብቶ የዲፕሎማ ትምህርቱን አጠናቋል፡፡

በተጨማሪም፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙኒዩኬሽን በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ ሲሆን፤ የሁለተኛ ዲግሪውንም በዚሁ ዩኒቨርስቲ በፊዚዎሎጂ አግኝቷል፡፡

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ ከመጋቢት 15 ቀን 1982 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወቱ እስካለፈበት እስከ መጋቢት አንድ ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአልዓለም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለ34 ዓመታት በተለያዩ የሥራ መደቦች አገልግሏል።

ከጥቅምት አንድ ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ሕይወቱ በድንገት እስካለፈባት መጋቢት አንድ ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስር በሚገኘው አልዓለም ጋዜጣ በዋና አዘጋጅነት ሀገሩን አገልግሏል፡፡

በተጨማሪም ጋዜጠኛ እዮብ ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ በአልዓለም ጋዜጣ አራሚነት በከፍተኛ ሪፖርተርነት፤ በሜክአፕ ኤዲተርነት፤ በከፍተኛ አዘጋጅነት፤ በምክትል ዋና አዘጋጅነት ሠርቷል።

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ በተለይ ለሙያው ካለው ልዩ ፍቅርና ክብር ላቅ ያለ በመሆኑ የሀገሩን ጥቅምና ክብር የሚያስጠብቁ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በዓረቡ ዓለም ጋዜጦችና ድረ-ገጾች ማሳተም ችሏል፡፡

በተለይ በኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያና ተያያዥ ሃገራዊ ጉዳዮች የትንታኔ ጽሑፎችን በመጻፍና በመሞገት ይታወቃል፡፡ ለአብነትም ለአራ ኩባ፣ ኑባ ታይምስ፣ አልሚሊንና ሱዳናይል የሱዳን መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም አል ዓረብ የኳታር ጋዜጦች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ጋዜጠኛ እዮብ ከወይዘሮ መሠረት ገብረማርያም ጋር ትዳር በመመሥረት ሁለት ልጆችንም አፍርቷል።

ጋዜጠኛ እዮብ ግደይ መጋቢት አንድ ቀን 2016 ዓ.ም በተወለደ በ58 ዓመቱ ባደረበት ድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱ የሚታወስ ነው፡፡

# የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መሠረተ ልማት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ በጋራ መኖሪያ ቤቶች መሠረተ ልማቶችን በጊዜው ለመገንባት አንዱና ዋነኛው ችግር የፋይናንስ እጥረት ነው፡፡ የኅብረተሰቡ ቁጠባ ሙሉ ቤቱን ይገነባዋል ማለት አይደለም፡፡ኅብረተሰቡ የሚቆጥበው 20 ወይም 40 በመቶ ነው፡፡ዛሬ ላይ ግንባታ በምን ያህል ወጭ እንደሚገነባ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

ከመንግሥት ወይም ከባንክ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ እዳ ውስጥ በመግባት ቤቶች እየተገነቡ ነው ያሉት ኢንጂነር ስጦታው፤ አሁን ካለው የግንባታ ዋጋ አንጻር ኅብረተሰቡ ምንም እንኳን መቆጠብ የሚገባውን መቆጠብ ቢችልም በቂ አይደለም ብለዋል፡፡በዚህም ምክንያት የፋይናንስ እጥረት ገጥሟል፡፡እጥረቱን ለመሙላት የፋይናንስ ምንጭ እየተፈለገ መሠረተ ልማት እንዲሟላና ቤቶቹ ምቹ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የተቋራጮች አቅም ውስንነት ሌላኛው ችግር መሆኑን የጠቆሙት ኢንጂነር ስጦታው፤ እንደሚታወቀው በጦርነት ውስጥ የቆየን በመሆኑ ተቋራጮች በቂ ሥራ እየሠሩ ስላልሆነ ለሠሩት ሥራ ጭምር የፋይናንስ ጥያቄ ሲጠይቁ ምላሽ መስጠት ባለመቻላችን ምክንያት በሙሉ አቅማቸው ሥራ እየሠሩ አይደለም ብለዋል፡፡

“በዚህ ምክንያት ክፍያ የሚጠባበቁ አሉ፡፡አቅም ያለው ተቋራጭ ሲሆን ሥራዎቹን በራሱ ገንዘብ አውጥቶ ሠርቶ አጠናቆ ክፍያውን ይጠብቃል፡፡አቅም የሌላቸው ግን በኮንትራታቸው መሠረት እየሠሩ ክፍያ ይጠብቃሉ፡፡ስለዚህ ሠርተው ክፍያ ካልተከፈላቸው ወደ ቀጣዩ ሥራ መግባት አይችሉም፡፡በዚህ ሳቢያ ችግሩ ሰፊ ነው” ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ኢንጂነር ስጦታው እንደገለጹት፤ አንዱ የመሠረተ ልማት ችግር ሊፍት ሲሆን አሁን ካለው የዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ ትልቅ በጀት የሚጠይቅ ነው፡፡ስለዚህ ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ጊዜ ወስዷል፡፡ነገር ግን አሁን ላይ አቅራቢዎቹ ውል ገብተው ባስቸኳይ ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ ስለሆነ በቀጣይ አንድ ወይም ሁለት ወር ውስጥ የሊፍት ወይም አሳንሰር ገጠማ ሥራ ይከናወናል፡፡

እንደ ኢንጂነሩ ገለጻ፤ አሁን ላይ ችግር ያለባቸው ቤቶችን በየሳይቱ ምን እንደጎደላቸው ተለይተው ችግሩን የመፍታት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከአራት ወለል በላይ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ውሃ ለማድረስ ፓምፕ ያስፈልገዋል፡፡ፓምፕ አሁን ላይ ጨረታ ላይ ስለሆነ ባሉት ቀጣይ ወራት ይገጠማል፡፡ሁለት ሺ በላይ ሕንፃዎች ስላሉ እነዚህን የሊፍት ባለቤትና የፓምፕ ባለቤት ማድረግ ቀላል ነገር ተደርጎ አይወሰድም ነው ያሉት፡፡

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከኢንጂነር ስጦታው አካለ ጋር ያደረግነውን ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ ዓምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የተጀመሩ የሠላም ጥረቶች ተጠናክረው ይቀጥሉ!

ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች የተጋረጡባት ሀገር ነች፡፡ ለሁለት ዓመታት ያህል በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተካሄደው ጦርነት ካሳረፈባት ቁስል ገና አላገገመችም፡፡ የአካባቢ መራቆት የፈጠረው ድርቅም እየፈተናት ነው፤ የኑሮ ውድነቱም ሌላው ፈተና ነው፡፡ ሥራ አጥነት ገና ያልተፈታ ችግር ነው፤ ለዘመናት የተከማቸ የዕዳ ጫናን መክፈልም እንዲሁ የዚህ ዘመን የቤት ሥራ ነው፡፡ እነዚህን ከግብ ለማድረስ ደግሞ ሠላም ያስፈልጋል፡፡

ሠላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው፡፡ ሠርቶ ለመኖር፤ በሀገር ለመኩራት፤ ወልዶ ለመሳም፤ ወጥቶ ለመግባት ሠላም ያስፈልጋል፡፡ ሠላም በሌለበት ነግዶ ማትረፍ፤ ተምሮ ለቁም ነገር መብቃት፤ በዜግነት መኩራትና የዕለት ተዕለት ኑሮን መምራት አዳጋች ነው፡፡ በአጠቃላይ ያለ ሠላም ሕይወት የምድር ሲኦል ናት፡፡

ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረውን ደም አፋሳሽ ጦርነት በሠላም ስምምነት እንዲቋጭ አድርጓል። «ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ» የሚለው የአሕጉራችን መርሕ በተግባር ተፈትሾ ውጤታማ እንደሆነ ማሳየት ተችሏል። ስምምነቶቹም ወደ ተግባር ተቀይረው መልሶ ግንባታ በመከናወን ላይ ነው ። ይህ ሂደት ለሀገራችን ብሎም ለአፍሪካ ትልቅ ትምህርት የሚወሰድበት ሆኖ አልፏል።

የሰሜኑን ጦርነት በንግግር ለመፍታት መቻሉ ብዙ ዜጎችን ከእልቂት እና ሰቆቃ የገላገለና እፎይታን የፈጠረ ነው። ከዚህም ባሻገር ከዚህ በኋላ በሀገራችን በጠብመንጃና በኃይል ልዩነቶችን የመፍታት አማራጭ ማክተም እንደሚኖርበትና እንደሚችልም በተግባር ያሳየ ነው። በዚህም መንግሥት ምንጊዜም ከማንኛውም ኃይል ጋር ችግሮችን በመወያየትና በንግግር የመፍታት ቁርጠኝነት እንዳለው በተግባር ያስመሰከረበት ነው።

መንግሥት ልክ እንደ ትግራይ ክልል ሁሉ በመላ ሀገሪቱ ሠላም ለማስፈንና የታጠቁ ኃይሎችም ወደ ሠላምና ወደ ልማት እንዲመለሱ ተደጋጋሚ ጥሪ በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

ሆኖም መንግሥት ባደረገው የሠላም ጥሪ እና ለሠላም ባለው ምኞት ልክ የተለያዩ አካላት ተገቢ ምላሽ ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ይልቁንም አንዳንዶች መንግሥት ለሠላም ያለውን ቀናዒነት በማጣጣልና እንደ ደካማነትም በመቁጠር በየጫካው ጦር ሲመዙ ታይተዋል፡፡ ሠላምንም ወደ ጎን በመተው ግጭትና ሁከትን አንግሠዋል፤ ጦርነትም በማወጅ ለበርካታ ዜጎች ዕልቂትና ለሠላም መደፍረስ ምክንያት ሆነዋል።

በየጫካና በየዱሩም ነፍጥ በሚያነሱ ቡድኖች ምክንያት አርሶ አደሩ ተረጋግቶ የእርሻ ሥራውን እንዳያከናውን፤ ገበሬው ነግዶ እንዳያተርፍ፤ ተማሪው በዕውቀት ገበታ ላይ እንዳይገኝ፤ ሰዎች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሰው እንዳይሠሩ ተደርገዋል፡፡ አልፎ ተርፎም ነፍጥ ባነሱ ቡድኖች አማካኝነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ አካል ጉዳተኛ ሆነዋል፤ ሕይወታቸውንም አጥተዋል፡፡

ስለሆነም ከግጭትና ጦርነት ምንም እንደማይገኝ አውቆ ፊትን ወደ ሠላም እና ልማት መመለስ ይገባል፡፡ ዛሬ ሥልጣን ለመያዝ ብረት ማንሳት አያስፈልግም፡፡ ብረት አንስቶ ጫካ ቢገባም ትርፉ ሕይወትን መገበር፤ ወጣቶችን ማስጨረስና ሀገርን ማዳከም እንጂ ሥልጣን በጠብመንጃ የሚያዝበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡

ዛሬ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚያስፈልገው የተሻለ ሃሳብ አምጥቶ ዕውቀትን ለገበያ ማቅረብ ብቻ ነው። በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ በመመካከርና በሃሳብ የበላይነት በማሸነፍ ያለሙትን ማሳካት ይቻላል። በሙሣሪያ ከማሸነፍ በሃሳብ የበላይነት ማሸነፍ ዛሬ ግዝፍ ነስቷል፡፡ ስለሆነም አማራጩ ፊትን ወደ ሠላምና ልማት መመለስ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር በአማራ እና በኦሮሚያ የተጀመሩ የሠላም ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡ ፡ በሁለቱ ክልሎች ሠላምን ማዕከል አድርገው እየተከናወኑ ያሉ ሕዝባዊ ውይይቶች ፍሬያቸው እየታየ በመሆኑ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ በቤኒሻንጉል፤ በጋምቤላ እና በደቡብ ምዕራብ የታየው ሠላምም ዘለቄታ እንዲኖረው ሁሉም አካላት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግሥትም የተጀመሩ የሠላም ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም ከታጠቁ ኃይሎች ጋር ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ያለው ቁርጠኝነት በውጤት እስኪታጀብ ድረስ ቀጣይነት ያለው ሊሆን ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መዳብ የሆኑብን፤ በእጃችን የያዝናቸው "ወርቆቻችን"

**ዳንኤል ዘነበ**

ከወራት በፊት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዘጋጅቶት የነበረን አንድ መድረክ ለመዘገብ ወደ ጅማ ከተማ አቅንቼ ነበር። በወቅቱ የመድረኩ አጋፋሪ በከተማው ነዋሪ ዘንድ ‹‹ፔሌ›› በሚል ቅፅል ስም የሚታወቁት አብዱልከሪም አባገሮ "በእንኳን ደህና መጣችሁ!" ንግግራቸው ስለ ጅማ ብዙ ቁምነገሮች እንዳነሱልንም አታውሳለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ጅማዎች ለእንግዳ ያላቸውን ክብር እና ትሕትና ስለ "ana cabsuu" ያነሱት ሃሳብ እጅጉን አስገርሞኝ ነበር፡፡

በአፋን ኦሮሞ "ana cabsuu " ትርጓሜው ስበረኝ እንደማለት ነው። የቤቱ ባለቤት "አናጨብሱ" ብሎ ወደ ቤቱ በአክብሮት የመጣው እንግዳ ከእሱ የሚበልጥ መሆኑንና በትሑት መንፈስ ፍቅሩን አክብሮቱን የሚያሳይበት የእንግዳ አቀባበል ሥርዓት ነው።

የአብዱልከሪም አባገሮ ንግግር ስሰማ ከመገረም ባለፈ ለካስ ኢትዮጵያውያን በአብሮነት፣ በአንድነት፣ በመከባበር፣ በመፈቃቀር.... ዘመናትን አብረው መኖር እንዲችሉ ያደረጓቸው፤ እንደ "አናጨብሱ" አይነት ማኅበራዊ እሴቶች ናቸው" የሚለውን እንዳሰላስል አድርጎኛል፡፡

ኢትዮጵያውያን እንደ "አናጨብሱ" አይነት ለእንግዳ ያላቸውን ክብር፣ ፍቅርንና ትሕትናን የሚያሳይበትና የሚያስመሰክሩበት በርካታ እሴቶች አሏቸው፡፡ በየዘመናት ሂደት በባሕል ውርርስና ልውውጥ ምክንያት ሕዝቦቿ የበርካታ ሀገር በቀል ዕውቀቶችና ጥበቦች ባለቤቶች ሆነዋል፡፡

ታሪክ ስንመረምርም ኢትዮጵያ ከዚህ የደረሰችው በረጅም የውስጥና የውጭ ፈተና አልፋ እንደሆነ እንረዳለን። ይሁንና ሁሉም በሚባል መልኩ አንገዳግደዋት ይሆናል እንጂ አልጣሏትም፡፡ ለዚህ ጥንካሬዋ ደግሞ በርካታ ምክንያቶችና ምርኩዞችን መዘርዘር ይቻላል።፡ እንደ "አናጨብሱ" አይነት ድንቅ ባሕላዊ እሴቶችም በተለይ በአንድነት ለመቀጠል ትልቅ አቅም እንደነበሩ መካድ የሚቻል አይደለም፡፡

በእኔ እምነት፤ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል የዚህ ድምር ውጤት ነው ። ለዚህ እንደ ማስረጃም፤ መስከረም 17 ቀን 1888 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ጣሊያን ለወረራ መሰማራቱን ተከትሎ ያስተላለፉት የክተት አዋጅን እናንሳ፡-

‹‹ ...ሀገር የሚያጠፋ፤ ሃይማኖትን የሚለውጥ፣ በፊት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል፡፡ እኔም የሀገሬን ከብት ማለቅ፤ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር፡፡ አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ ....ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በኃዘንህ እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ። አልምርህም፡፡ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም።›› ሲሉ አዋጅ አስነገሩ ።

በወቅቱ አኩርፈው የነበሩ ንጉሦች አሻፈረኝ ብለው አኩርፈው አልቀሩም። ለሀገር ፍቅርና ክብር፣ ለእምነት፣ ለመሬት፤ ለንጉሥ ከፍ ያለ ክብር ይሰጣል። በሀገራችን በሁሉም ማኅበረሰብ ዘንድ መሪ ይደመጣል፤ ይከበራል፣ ይፈራልም። የሀገር ክብር ከቁርሾም በላይ ነበርና፤ የንጉሡን ጥሪ አሻፈረኝ ብሎ የቀረ አልነበረም። በጊዜው በንጉሡ ላይ ጥያቄ የነበራቸው ጥያቄያቸውን በይደር አስቀምጠው ለሀገር ሉዓላዊነት በአንድነት ቆመዋል።

ታላቅን ማክበር፣ መደማመጥ፣ ለአባቶች ቦታ መስጠት፣ እርቅ መፈጸም፣ መታዘዝ፣ መረዳዳትና መሰል የሥነ ምግባር መርሆዎች የኢትዮጵያውያን የጋራ እሴቶች ናቸው። አባቶቻችን ይህን በመሰለ በጎ እሴት እጅ ለእጅ ተያይዘው ችግሮችን አልፈው ኢትዮጵያን ማጽናት ችለዋል።

አባቶቻችን እነዚህን የወል እሴቶች በመጠቀም ችግሮችን ፈትቶና አስታርቆ፤ የተበላሸን አቅንቶ፤ የነገውን መልካም ተስፋ አሳይቶ በይቅርታና በፍቅር መኖር እንደሚቻል አሳይተውናል። አሁንም በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ለሠላም፣ ለአብሮነት ፋይዳ ያላቸው አንድነትን የሚያጠናክሩ የመከባበር፤ አብሮ የመብላትና የመሥራት ዕሴቶች ግጭቶች እንዳይከሰቱ ወይም እንዳይባባሱ የማድረግ አቅም ያላቸው ባሕላዊ እሴቶች አሉ።

> ኢትዮጵያውያን እንደ "አናጨብሱ" አይነት ለእንግዳ ያላቸውን ክብር፣ ፍቅርንና ትሕትናን የሚያሳይበትና የሚያስመሰክሩበት በርካታ እሴቶች አሏቸው

ምናልባትም ቢደበዝዙ እንጂ ጨርሶ አልጠፉም ማለት ይቻላል፡፡ "የጋሞዎች እርጥብ ሣር " ገድልም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ነው፡፡

የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ለበቀል ተነስቶ የነበረውን የአርባ ምንጭና የአካባቢውን ወጣት ለምለም ሣር ይዘው ተንበርክከው በመለመን ቁጣውን አብርደው መልሰውታል። ይህን የሀገር ሽማግሌዎች ገድል በጥሞና ለተረዳው የአርባ ምንጩን እሳት ብቻ አይደለም ያጠፉት፤ ጥፋቱን ተከትሎ ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ሊዛመት የነበረውን የበቀል ሰደድ እሳት ጭምር እንጂ ።

ከስተቱና ቁጣ አብራጁ የጋሞ አባቶች ልመናም ከፍ ብሎ ሊገለጥ የሚገባው የትላንት ባሕላዊ የግጭት አፈታት፣ የእርቅ አውርድ እና የፍቅር ማስፈኛ አቅማችን ብሎም ጥበባችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ከምንም በላይ ጥሩ ማሳያ መሆን የሚችል ነው፡፡

ባሕላዊ ወረታችን ለበጎ ዓላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት፣ የሰው ልጆችንም ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል። እነዚህ የባሕል እሴቶች ትኩረት ቢያገኙ እንደ ሀገር ያሉብንን አለመግባባቶች፣ ያሉብንን ስብራቶች "የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ እንደሚባለው" መጠገን ይችላሉ የሚል ጽኑ እምነት አለኝ።

ኢትዮጵያን እንደ ሀገር እየፈተኗት የሚገኙ አስቸጋሪና እጅግ አሳሳቢ ችግሮች መኖራቸው ይታወቃል። ከሚበቃት በላይም ጦርነቶች የተካሄዱባት ሀገር መሆኗን፣ የታሪክ ድርሳናትን በማገላበጥ መረዳት ይቻላል፡፡ የድህነትና የኋላቀርነት መፈንጫ የሆነችውም ሠላሟ እየተናጋ መረጋጋት በመጥፋቱ ነበር፡፡ ዛሬም በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች አሉ። የፖለቲካ ዝለት ብቻም ሳይሆን፣ ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ከሚደረግ ጥረት ይልቅ ጠመንጃን ዋነኛ አማራጭ አድርጎ የመቁጠር አስተሳሰብ ጎልብቷል።

ይሑንና በመሰል አካሄድ አባቶቻችን በጥበብ ያቆዩልንን ሀገር እኛ በስሜት ለማፍረስ መሽቀዳደም የለብንም። ለመነጋገርና ለመደማመጥ ቦታ አለመስጠት መዘዙ የከፋ በመሆኑ፤ ከዚያ ዓይነቱ አስከፊ አዙሪት ውስጥ መውጣት ያስፈልጋል፡፡ በ"አናጨብሱ" ባሕልና ትውፊት በተቃኘ መልኩ በመደማመጥ፣ በመከባበር፣ በመነጋገር የሠላምንና የዕርቅን ባንዲራ ከፍ ማድረግ ይኖርብናል። በትሕትና ዝቅ ማለትና በፍቅር የመሸነፍ የ'አናጨብሱ' ባሕል በፖለቲካችን መድረክም ሥፍራ ቢያገኝ አትራፊ እንሆናለን ።

በኢትዮጵያ እዚህም እዚያም የሚስተዋሉ ችግሮችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድም፤ የተጣሉ የሚታረቁበት፣ አብሮነት በጉልህ የሚንጸባረቅባቸው የጋራ እሴቶቻችንን እንደ ዋነኛ አማራጭ መጠቀም ተገቢ ይሆናል። በዚህም ኅብረተሰቡን በማሳተፍ የቆዩ ሀገራዊ የጋራ እሴቶችና ልምዶች ቀምሮ ወደ ተግባር መግባት አስፈላጊ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ የታለመለትን ግብ እንዲያሳካ በየአካባቢው ያሉ ባሕላዊ እሴቶቻችንን መጠቀም ይኖርብናል። ስለሆነም በእጃችን ያሉት ወርቅ የሆኑት የወል እሴቶቻችን መዳብ እንዳይሆኑብን በልካቸው ተገንዝበንና ተጠቅመን ሀገርን ማጽኛ ልናደርጋቸው ይገባል።

# ተጠየቅ



## «እድለኞች ወደ ቤታቸው የገቡት ሁሉ ነገር ተሟልቶ እና ምቹ ሆኖ አይደለም»

- ኢንጂነር ስጦታው አካለ
የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ

**የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ከሚገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች መካከል፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች/ኮንዶሚኒዬም ቤቶች ሲሆኑ፤ ይህም ነዋሪዎች እየቆጠቡ ቤት ለማግኘት ተመዝግበው የሚጠባበቁበት ነው፡፡ ሆኖም በተለያዩ ወቅቶች ተገንብተው ለባለዕድለኞች በዕጣ የሚተላለፉ እነዚህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እንደ መብራት፤ መንገድ፤ ውሃ፤ አሳንሰርና መሰል የመሰረተ ልማት አለመሟላት ችግር፤ እንዲሁም የጥራት ጉድለት እንዳለባቸው ቅሬታዎች ሲነሱ ይደመጣል፡፡**

**ይሁን እንጂ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ከተጠናቀቁ በኋላ ለባለዕድለኛ ከመተላለፋቸው በፊት ከላይ የተጠቀሱት የመሰረተ ልማት አውታሮች ተሟልተው እንደሚተላለፉ መመሪያው ላይ ተቀምጧል። ነገር ግን እንደ ቦሌ በሻሌና መሰል የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከአምስት ዓመት በፊት ለነዋሪዎቻቸው በዕጣ የተላለፉ ቤቶች መሰረተ ልማት ያልተሟሉባቸው ናቸው፡፡ ይሄም ለባለእድለኞች የመልካም አስተዳደር ችግር ብቻ ሳይሆን፤ ላልተገባ ወጪ መዳረግ ምክንያት ሆኗል።፡**

**እኛም ለዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን በእነዚህና ሌሎችም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎችን መነሻ በማድረግ ያዘጋጀን ሲሆን፤ በዚህም በጋራ መኖሪያ ቤቶች ግባታና የመሰረተ ልማት አቀርቦት ችግር ምክንያቶች፣ ችግሮቹን በምን መልኩ እየተፈቱ እንደሆነና መሰል ጉዳዮችን በማንሳት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ስጦታው አካለ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ምንባብ፡፡!**

**አዲስ ዘመን፡- በተለያዩ ችግሮች ከአምስት ዓመታት በላይ ነዋሪዎች ያልገቡባቸው በርካታ ቤቶች አሉ፡፡ በከተማው ክፍተኛ የመኖሪያ ቤት ችግር ባለበት ሁኔታ ይህ ከአሰራር አንጻር እንዴት ይታያል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** ነዋሪዎች እጣ ካወጡበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ቤታቸው እንዲገቡ በአስተዳደሩ በኩል በርካታ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም፤ አሁንም ድረስ ያልገቡ የቤት እድለኞች እንዳሉ ይታወቃል። ይህም ከመሰረተ ልማት ጋር የተያያዘ ነው ፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ ዋና ዋና የሚባሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች የማሟላት ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመሰረተ ልማቶችን ለማሟላት በርካታ ችግሮች መኖራቸውን መውሰድ ተገቢ ነው ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በርካታ የተባሉት ችግሮች የትኞቹ ናቸው? እንዴትስ ለመፍታት ታስቧል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** አንዱና ዋነኛው ችግር የፋይናንስ ዕጥረት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የኅብረተሰቡ ቁጠባ ሙሉ ቤቶችን ይገነባል ማለት አይደለም፡፡ ኅብረተሰቡ የሚቆጥበው 20 ወይም 40 በመቶ ነው፡፡ ዛሬ ላይ ግንባታ በምን ያህል ወጭ እንደሚገነባ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ከመንግስት ወይም ከባንክ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ እዳ ውስጥ ገብተን ነው ቤት እየገነባን ያለነው፡፡

አሁን ካለው የግንባታ ዋጋ አንጻር ኅብረተሰቡ ምንም እንኳን መቆጠብ የሚገባውን መቆጠብ ቢችል እንኳን በቂ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የፋይናንስ እጥረት ገጥሟል፡፡ እጥረቱን ለመሙላት የፋይናንስ ምንጭ እየተፈለገ መሰረተ ልማት እንዲሟላና ቤቶቹ ምቹ እንዲሆኑ የቀሩት ቤቶች እንዲጠናቀቁ የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አሁን ላይ አጫጭር እቅዶች ታቅደዋል። ችግር ያለባቸው ቤቶችን በየሳይቱ ምን እንደጎደላቸው ተለይተው ችግሩን የመፍታት ስራ 24/7 እየተሰራ ነው። በዚህም ኅብረተሰቡ ወደ ቤቱ መግባት የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ሆኖም ውስን ብሎኮች የሚቀሩ ሲሆን፤ በተያዘው ወር ይጠናቀቃል፡፡

ሌላው ችግር የተቋራጮች አቅም ውስንነት ነው። እንደሚታወቀው በጦርነት ውስጥ የቆየን ስለሆነ ተቋራጮች በቂ ስራ እየሰሩ ስላልሆነ ለሰሩት ስራ ጭምር የፋይናንስ ጥያቄ ሲጠይቁ ምላሽ መስጠት ባለመቻላችን ምክንያት በሙሉ አቅማቸው ስራ እየሰሩ አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ክፍያ የሚጠባበቁ አሉ፡፡ አቅም ያለው ተቋራጭ ሲሆን ስራዎቹን በራሱ ገንዘብ አውጥቶ ሰርቶ አጠናቆ ክፍያውን ይጠብቃል፡፡

አቅም የሌላቸው ግን በኮንትራታቸው መሰረት እየሰሩ ክፍያ ይጠብቃሉ፡፡ ስለዚህ ሰርተው ክፍያ ካልተከፈላቸው ወደ ቀጣዩ ስራ መግባት አይችሉም። ከዚህ አኳያ ችግሩ ሰፊ ነው፡፡ የፋይናንስ እጥረቱ በእኛ ላይ ብቻ ሳይሆን በተቋራጮች አቅም ላይ ጫና ፈጥሯል፡፡

ሌላኛው፣ በኅብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ ስራዎች አሉ፡፡ ሁሉም ስራ በመንግስት የሚሰራና የሚጠናቀቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ኅብረተሰቡ ራሱ ቤቱ ከተሰራለት ገብቶ ማልማት በጋራና በትብብር መስራትን ይጠይቃል። በርካታ ስራዎችን ሰርተን አጠናቀን ነዋሪዎች ገብተው የሚያለሟቸው ስራዎች ይጠበቃሉ፡፡ በዚህ ላይም መስራት ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ችግሩ ከሚታይባቸው የጋራ መኖሪያ ሳይቶች መካከል የቦሌ በሻሌ ሳይት ነው። በዚህ ሳይት እንደ ውሃ መብራት፤ አሳሰንሰርና መሳሰል መሰረተ ልማቶች አልተሟሉም፡፡ ነገር ግን በ2011 በዕጣ ለነዋሪዎች የተላለፉ ቤቶች ናቸውና መሰረተ ልማቶች ሳይሟሉ የሚተላለፉበት አሰራር አለ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** የቦሌ በሻሌ ሳይት ከሌሎች ሳይቶች የተሻለ ሳይት ነው፡፡ ነገር ግን የጎደሉት ነገሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ ሊፍት ሲሆን፤ ይሄን በቀጣይ የምናስተካክለው ነው። ሆኖም አሁን ካለው የዋጋ ንረት በተያዘ ትልቅ በጀት የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ጊዜ ወስዷል፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ አቅራቢዎቹ ውል ገብተው ባስቸኳይ ወደ አገር ውስጥ እየገባ ስለሆነ በቀጣይ አንድ ወይም ሁለት ወር ውስጥ የሊፍት ወይም አሳንሰር ገጠማ ስራ ይከናወናል፡፡

ሌላው ከውሃ ጋር ተያይዞ ብዙ ወለሎች ያሉት ሕንጻ ስለሆነ ፓምፕ ያስፈልገዋል፡፡ ፓምፕ አሁን ላይ ጨረታ ላይ ስለሆነ ባሉት ቀጣይ ወራት ይገጠማል። በሳይቱ ከሁለት ሺህ በላይ ሕንጻዎች ስላሉ እነዚህን የሊፍት ባለቤትና የፓምፕ ባለቤት ማድረግ ቀላል ነገር ተደርጎ አይወሰድም፡፡

ከዚህ ውጪ ከመንገድ አኳያ ውስጥ ለውስጥ ጭምር አስፓልት ሆኗል፡፡ የእግረኛና የመብራት መስመር አለው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሳይት የጎደሉ ነገሮች አይሟሉም ማለት አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ባስቸኳይና ባጠረ ቀን ውስጥ የሚሟሉ ናቸው፡፡ ከፍሳሽ ጋር ትናንሽ መስመሮችን የማገናኘት ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ከእያንዳንዱ ብሎክ ያለው የፍሳሽ መስመር ካልተገናኘ ፍሳሽ ማስተናገድ አይቻልም፡፡ እነዚህ ፍሳሾች መስተናገድ የሚችሉት የፍሳሽ መስመሮችን ከሰራን በኋላ የሚገናኝ በመሆኑ እየተሰራ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ቀሪ ስራዎችን በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡ አመራሩ ችግር የሚስተዋልባቸውን ግንባታዎች የክትትል ስርዓት በመዘርጋት እየሰራ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ነዋሪው እየቆጠበ ያለው ከ15 ዓመት በፊት በነበረው ዋጋ በመሆኑ አሁን ላይ ያለው የግንባታ ወጭ ከሚቆጥበው ዋጋ ጋር የሚመጣጠን አይደለም። ለምሳሌ፣ የሚቆጠበው ከሁለት መቶ ሺ እስከ 400 ሺ ብር ድረስ ነው፡፡ መቶ ሺህ ብር የቆጠበ ሰው ባለ ሶስት መኝታ ቤት እንዲደርሰው ይጠብቃል፡፡ እንደ ደረሰው ቤቱ ጥንቅቅ ብሎ አልቆ ቁልፍ ተረክቦ ወደ ቤቱ መግባት ይፈልጋል፡፡ በመቶ ሺ ብር ግን ቤቱ አይገነባም። ነገርግን እንደ ሀገር የገጠመንን ፋይናንስ ቀውስ በመቆጣጠር መንግስትም በብዙ ጫናዎች ውስጥ ሆኖ ቤቱ የሚያልቅበትን ብድር ጭምር እያመቻቸ ችግሩን የሚመጥን ስራ እየሰራ ነው፡፡

ስለዚህ ጊዜ የወሰደው በምክንያት ነው፡፡ እንዲሁ ቤት ለምን አላገኝም የሚል ቀላል ጥያቄ ይሰማል። ይህ እውነታውን ካለመገንዘብ የመጣ ነው፡፡ ቤቶቹ የሚተላለፉበት ዋጋም ከፍተኛው አምስት መቶ ሺህና ስድስት መቶ ሺህ ብር ነው፡፡ በግል ቤት ልማት ግባታ የተሰማራ ባለሀብት ቤቱን በስንት ሚሊዮን ብር እንደሚሰጥ ማሰብ ነው፡፡ ከ12 እስከ 15 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ስለዚህ ቀሪውን ገንዘብ መንግስት እየደጎመ እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡

ይህም እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ የሚረጭ ሳይሆን ቅድሚያ በመስጠት የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስትና የግል አጋርነትን የመሳሰሉ በሌሎች አማራጮች ጭምር ቤቶችን ለመገንባት እየተሰራ ነው። የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግር ያለባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች በጥቂት ወራት ይጠናቀቃሉ፡፡ የመንገድ ግንባታ ችግር ያለባቸው እንደ ሀያት ሁለት እና መሰል ሳይቶች እስከ ሰኔ ድረስ ተገንብተው ማጠናቀቅ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለባለ ዕድለኞች ከመተላለፋቸው በፊት የሚተላለፉበት መመሪያ ምን ይላል፤ በመንግስት በኩል መሟላት ያለባቸው መሰረተ ልማት የትኞቹ ናቸው? ከባለዕድለኞችስ ምን ይጠበቃል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** ከተማ አስተዳደሩ የሚገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለባለዕለኞች ከመተላለፋቸው በፊት ምን ምን ነገሮች መሟላት እንዳለባው በግልጽ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ሁሉንም መሰረተ ልማቶች ማሟላት ግዴታ አለበት፡፡ ለመኖሪያ ምቹ የማድረግ ጉዳይ የግድ ነው፡፡ ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ገብቶ ለመኖር ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን በብዙ ምክምያቶች ሳይሟሉ የሚቀሩ መሰረተ ልማቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የሕንጻው አስገዳጅ አዋጅ የሚያመላክት ነው "አራት ወለለል እና ከዛ በላይ የሆኑ ሕንጻዎች ሊፍት የግድ" መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ማድረግ አልቻልንም፡፡ ሕንጻዎቻችን ከአራት ወለል በላይ ናቸው። ነገር ግን ጥቂት ጊዚያት ቢዘገይ ማኅበረሰቡ ችግሩን ተቋቁሞ ሌሎች አማራጮችን ተጠቅሞ መንግስትም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሆነ ተገንዝቦ መሰረተ ልማቱ እስኪገባ ድረስ መጠበቅ ግዴታ ሆኗል ማለት ነው፡፡

ከተማ አስተዳደሩም ከአቅሙ በላይ ባይሆን ኖሮ የሊፍት ጉዳዮችን ችላ እንደማይል መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ እጣ ቀድሞ ሊወጣ ይችላል፡፡ ዕጣው በሚወጣበት ወቅት ታሳቢ የሚደረገው ቤቶቹ መጠናቃቸውን ነው። መሰረተ ልማቶቹ ላይሟሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በሂደት ዕጣ ከወጣባቸው ጊዜ ጀምሮ ቀሪ ስራዎች በፍጥነትና ባጠረ ጊዜ ውስጥ ኅብረተሰቡ እስኪገባ ድረስ ጎን ለጎን እናለማለን በሚል የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በታሰበው ልክ ያልተሰራ ስራ እንዳለ ተገንዝበናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የጋራ መኖሪ ቤቶች የግንባታ ጥራት ጉድለት እንዳለበት የአፍሪካ ከተሞች የምርምር ጥምረትና ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የተሰኙ ተቋማት በጋራ ባደረጉት ጥናት ይፋ አድርገዋል፤ በኅብረተሰቡም ችግሩ እንዳለ ይነሳል፤ በጉዳዩ ላይ ምን ይላሉ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** የጥራትን ጉዳይ በምንም ሁኔታ ችላ የሚባል አይደለም፡፡ የጥራት ወይም የደህንነት ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ግንባታዎች እንዲፈርሱ እያደረግን ነው፡፡ ተቋራጮችን ተጠያቂ እያደርግን ነው፡፡ ክፍተትና የጥራት ችግር የፈጠሩትን ተቋራጮችን ተጠያቂ እየተደረጉ ነው፡፡ ወደ ግንባታው የሚገቡ ግብዓቶን እንደ አፈር፤ ብረት፤ ሲሚንቶና ሌሎች ግብዓቶች ጭምር እየተፈተሸን ነው፡፡ አንዳንዶችን ግብዓቶች ደግሞ መንግስት በራሱ ያቀርባል፡፡ ይሁን እንጂ የጥራት ችግር አይኖርም ማለት አይደለም፤ በሚሰራው የክትትል ስራ ግኝት ግን እርምጃ እየወሰድን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በተጨባጭ የተወሰደ እርምጃ ምንድን ነው?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** በጣም፡፡ በበርካታ ተቋ ራጮች ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ እርምጃቸው ግን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## «እድለኞች ወደ ቤታቸው...

ከገጽ 6 የዞረ



በተለያየ ደረጃ የተከናወነ ነው፡፡ የውል ማቋረጥ፤ የገነባው እንዲፈረስ ማድረግ እስከ ማገድ ድረስ የዘለቀ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች የተለያዩ ሳይቶች ከአሳንሰር፣ ውሃ፣ መብራት እና መሰል መሰረተ ልማት ችግሮች አሉ፡፡ ይህም የቅንጅት ክፍተት እንዳለ አመላካች ነው፡፡ ውሃ፣ መብራትና መንገድ የቅንጅት ስራው መስራት ላይ ምን ይመስላል? ችግሩ መኖሩን ታምናላችሁ?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** በየሳይቶቹ ያሉ ቀሪ ስራዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ከሊፍት ጀምሮ የአሉሚኒየም ስራዎች አሉ፡፡ በተለይ 40/60 ዎቹ ላይ የበር፤ የመብራት፤ የፓምፕ፤ የውሃ የፍሳሽ ማስወገጃ የመስመር ዝርጋታ ስራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ዘርፉ በሚመለከታቸው ተቋማት የሚሰሩ ናቸው፡፡ መሰረተ ልማቶቹ በእነዚህ መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት የሚገነቡ ናቸው፡፡

ቅንጅትን በተመለከተ አቀናጅ መስሪያ ቤት አለ፡፡ ስለዚህ በዚህ ተቋም ስር ይገመገማል፤ በስሩ እየተመራ በሚመለከታቸው የመሰረተ ልማት አልሚዎች ጋር እየተከናወነ ነው፡፡ አሁን የምታነሳልኝ ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ከመሰረተ ልማት ጋር የተያያዙ ናቸው። ይሁን እንጂ እኛ እንደቤቶች አስተዳደር ቤቱን ገንብተን ጨርሰናል፤ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች እኛን አይመለከተንም ሂዱና የሚመለከታቸውን ተቋማት ጠይቁ አላልንም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የጋራ ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እንደ መንግስት በመሰናሰል እና በመቀናጀት መስራት የግድ ነው፡፡ ቅንጅታዊ አሰራሮችን ተከትለን ቀሪ ነገሮችን ለማሟላት ከተለያዩ ተቋማት ጋር ተናበን እየሰራን ነው፡፡

በውጭ ምንዛሬ፣ በበጀት እና በእቅድ ችግር ተቋማት ባሰቡት ልክ ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን እንደ መንግስት ተቋም አንዱ ተቋም ሌላኛውን ተቋም ይጠብቃል፡፡ ለምሳሌ፣ መንገድ መብራት እና ውሃን ሊጠብቅ ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ሁሉም ተቋማት የጋራ ኃላፊነቶች አሉባቸው፡፡ ለመዘግየቱ አንዱ ተቋም በሌላኛው ተቋም ማሳበቡ ለነዋሪው አይጠቅምም፡፡ የሁሉም ተቋማት ችግሮች የእኛ ናቸው ብሎ ወስዶ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገዶች መፈለግ ይሻላል፡፡

አሁን ላይ በነባር ሳይቶች የነበሩ የመሰረተ ልማት ትያቄዎች ሁሉንም ብሎ መናገር በሚያስችል ተፈተዋል። በጣም ጥቃቅን የማጠናቀቂያ ስራዎች ብቻ ናቸው የቀሩት፡፡ አሁን ደግሞ በሚቀጥሉት ወራቶች ሊፍት ከገጠምን ለመጨረስ እየሰራን ነው፡፡ "ፓንፕን" በተመለከተ ጨረታ አልቆ ቀርቧል፡፡ ስለዚህ የሚቀር ነገር የለም ማለት ነው፡፡ መንገድም በተመለከተ እንዲሁ መውጫ መግቢያ መንገድ ብቻ ሳይሆን አስፋልት ጭምር ተሰርቷል፡፡ ስለዚህ ነባር ሳይቶች ጥሩ የመኖሪያ መንደሮች በሚሆኑበት ልክ ዝግጁ እየሆኑ ነው፡፡ ቀሪ ነገሮችን ለማጠናቀቅ ቀንም ምሽትም 7/24 እየሰራን ነው፤ አሁንም እንሰራለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ መብራት የሰራውን መንገድ፣ መንገድ የሰራውን ውሃ፤ ወዘተ ሲያፈርሱ ይስተዋላል፡፡ ይህ ደግሞ ተናቦ አለመስራትን ያመለክታል፡፡ እናንተ በቅንጅት መስራታቸውን እንዴት ነው የምታረጋግጡት?**

**ኢንጅነር ስጦታው፡-** አሁን እንደዚያ አይነት አሰራር የለም፡፡ አንዱ የአንዱን የመሰረተ ልማት አፍርሶ የራሱን መሰረተ ልማት መገንባት አይችልም፡፡ አሁን ላይ ያስጠይቃል፡፡ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ስታንዳርድ አለው፡፡ በስታንዳርዱ እንዴት አብረው መስራት እንዳለባቸው፣ መቼ ምን መስራት እንዳለባቸው ተቀምጧል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ በ2016 ዓ.ም የመጀመሪያ ወር ላይ የጋራ እቅድ አውጥተን፤ ተፈራርምን፡፡ ለምሳሌ፣ በዚህ ዓመት በአንድ ሳይት ላይ የመብራት፣ ውሃ፣ ኢትዮ ቴሌኮም ሌሎችም መሰረተ ልማቶች እንሰራለን ብለን ካቀድን ሁሉም ተቋም እቅዱን ወደ ተቋሙ ይወስዳል፡፡ ስለሚሰራው ስራ ዲዛይን ያዘጋጃል፤ በጀት ያዘጋጃል፡ በእቅዱ መሰረት ገብቶ ይሰራል፡፡ ስለዚህ አሁን ምን አልባት አንዱ አንዱን መጠበቅ ካልሆነ በስተቀር እና በተለያዩ ችግሮች በስተቀር አንዱ አንዱ የመሰረተ ልማቶች የሚያፈርስበት መንገድ አስቀርተናል፡፡

አሁን ያለው ችግር መጠባበቅ ብቻ ነው። መጠባበቁ ደግሞ ሆን ተብሎ የመጣ አይደለም። በተለያዩ ከተቋማቱ አቅም በላይ በሆኑ ችግሮች ምክንያት የሚፈጠር፡፡ አንዱ የተሰጠውን ስራ ካልጨረሰ ሌሎቹ ደግሞ መስራት አይችሉም፤ ቆመው የዘገየውን ይጠብቃሉ፡፡ የግድ ስለሆነ። ነገር ግን በፊት እንደነበረው አንዱ የሰራውን መሰረተ ልማት አንዱ አፍርሶ ሲካሰሱ እና ፍርድ ቤት ለፍርድ ቤት የሚያባክኑትን ሰዓት አስቀርተናል። ስራዎችን የምንገመግምበት የጋራ ፕላት ፎርም አለን። በወር አንድ ጊዜ ስራዎችን እና አፈጻጸማቸውን እንገመግማለን፡፡

ቴክኒካል ኮሚቴው በየሳምንቱ እና በየ15 ቀኑ ሳይት ላይ ወርዶ የሚሰሩ ስራዎችን ያያል፤ ይገመግማል፡፡ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተው ሪፖርት ያደርጋል። ስለዚህ የተቋም ኃላፊዎቹ ሁኔታውን ወይም ስራዎች እንዴት እየሄዱ ነው? የሚለውን በወር አንድ ጊዜ እንገመግማለን፡፡ ማን ምን ችግር ፈታ? ማን ምን ጨረሰ? ምን ቀረው? የሚለውን በጋራ እናያለን፡፡ በዚህም የተቀናጀ አካሄድ መሰረተ ልማት የማቅረቡን ስራ በተገቢው ሁኔታ እየተመራ ነው፡፡

ነገር ግን አሁንም የተለያዩ ምክንያቶች መሰረተ ልማት ማቅረብ ያልቻሉበት ሁኔታ ስላለ እሱን በቀጣይ እየገመገምን የምናስተካክለው ይሆናል፡፡ ምን አልባትም ካቅማችን ባላይ ከሆነ የበላይ አካላት ጭምር እያማከርን እየፈታን የምንሄድ ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ነባርም ሆነ አዲስ በተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እጣ የወጣላቸው ዜጎች ምን ያህል ወደቤታቸው ገብተዋል?**

**ኢንጅነር ስጦታው፡-** በመገንባት ላይ ከነበሩ አጠቃላይ 139 ሺህ ቤቶች ውስጥ 130 ሺህ ያህሉ ተጠናቀው እስከ ሰኔ 30 2015 ዓ.ም ድረስ እድለኞች ቤታቸው ገብተዋል፡፡ ባንድም በሌላ፣ ወደ ቤቶቹ ሰው ላይገባ ይችላል፡፡ ነገር ግን ቤቶቹ ለመኖሪያ ምቹ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ግንባታቸው ሳይጠናቀቅ ወደ 2016 ዓ.ም የተሻገሩት 7 ሺ ገደማ ቤቶች ነበሩ፡፡ ከእነኚህ ውስጥ አሁን ላይ አብዛኛዎቹን ጨርሰናል፡፡ ይህም የዘገየው በበጀት ችግር ነበር፡፡

አሁን ላይ ሰዎች ገብተው ቤታቸውን እያደሱ ነው፡፡ አሁንም አያት ሁለት የቀሩ ቤቶች አሉ፡፡ በሚቀጥሉት ወራት እነሱን ለማስገባት እየሰራን ነው። በጀት ተመድቧል፡፡ ተቋራጮችን፣ ማኅበራቶችን፣ የነዋሪ ማኅበራትን፣ የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማትን አወያይተናል፡፡ ችግሮቹ እንዴት ይፈቱ? የሚለውን ገምግመናል፡፡ እንዴት ይሰሩ? የሚለው ላይ ተግባብተናል፡፡ በሚቀጥሉት ወራቶች ችግሮች አሉባቸው የምንላቸው ሳይቶች ችግራቸው ተፈቶ የቤት እድለኞች ወደቤታቸው ይገባሉ የሚል ግምገማ ነው ያለን ፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- በበርካታ ሳይቶች ሊፍት እና መሰል መሰረተ ልማቶች ባለመኖራቸው ልጆቻቸውን ለሰራተኛ ከፍለው በሸኮኮ የሚያስወጡ አሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ወደቤታቸው የገቡት ሰዎች ለመኖር ተመችቷቸዋል ለማለት ያስደፍራል?**

**ኢንጅነር ስጦታው፡-** ልክ ነህ፤ እድለኞች ወደቤታቸው የገቡት ሁሉ ነገር ተሟልቶ እና ምቹ ሆኖ አይደለም፡፡ ሊፍት በሌለበት ምቹ ነው ልንል አንችልም። ግን ከአዲስ አበባ የነሮ ውድነት፤ በከተማችን ላይ ካለው የቤት እጥረት አንጻር ሰዎች ቤታቸው ገብተው እየኖሩ ነው፡፡ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አረንጓዴ ስፍራ፣ የልጆች መጫወቻ፣ በቅርብ የሚገኝ የልጆች ትምህርት ቤት እና መሰል ነገሮች ለማሟላት በከተማ አስተዳደሩ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ሲሟሉ ነው ምቹ ነው ልንል የምንችለው፡፡ እነዚህ ባልተሟሉበት ምቹ ልንል አንችልም፡፡

ነገር ግን በከተማችን ካለው የቤት ችግር አንጻር በእጅጉ የቤትን ችግር የሚያቃልል መሆኑን ታሳቢ ተደርጎ የቀሩ ነገሮችን በፍጥነት እንዲሟሉ ለማድረግ ኅብረተሰቡን እያሳተፍን እየሰራን ነው፡፡ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ ሲባል ገንዘብ ብቻ አይደለም፡፡ በጉልበትም መሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በትብብር መልክ አካባቢውን የማጽዳት፣ ምቹ የማድረግ ጉዳይ በመንግስት ብቻ የሚሸፈን እንዳልሆነ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መሰረተ ልማቶች ተሟልተው ቤታቸው ያልገቡ ሰዎች የግድግዳ እና የጣሪያ ግብር እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ይህን እንዴት ይገመግሙታል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** የግብር ጉዳይ ከአገልግሎት ጋር አይገናኝም፡፡ ባለእድለኛው ሀብቱ የእነሱ ነው፤ ንብረቱ የእነሱ ነው፣ ያ ቤት የተገነባው ለእነሱ ነው፣ በስማቸውም ውል ተዋውለዋል፡፡ በስማቸው ውል ከተዋዋሉባት ጊዜ ጀምሮ ያ ቤት የእነሱ ነው፡፡ ቀሪ እዳ ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ለዚያ ሀብት ደግሞ የግድግዳ እና የጣሪያ ግብር መገበር ግዴታ ነው፡፡ ሀገራዊ ኃላፊነትም ነው፡፡ ግብር ካልተሰበሰበ ለሌሎች በምንስ ይሰራል?

**አዲስ ዘመን ፡- የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች ቤታቸውን እስከምን ድረስ ማልማት ይችላሉ? አፍርሰው እንደገና መስራት ይችላሉ? መመሪያው ምን ይላል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** ቤት ተረክበው ከገቡ በኋላ በተወሰነ ደረጃ ውስጥ ላይ "ኢንቴሬር ዲዛይን" ሰርተው ለራሳቸው በሚመቻቸው መልኩ አስተካክለው ሲሰሩ እያየን ነው፡፡ ዋናውን የቤት ስትራክቸር ሳይነኩ የውስጥ ፓርቲሽን የማስተካከል ስራ አይከለከልም። መንግስት በብዙ ሚሊዮኖች ያወጣበትን ግንባታ አፍርሰው መገንባት ግን አይችሉም፡፡ ነገር ግን ሰው በአቅሙ እና በሚመቸው ልክ ሊያድስ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በእድሳት ወቅት የሚያስወግዳቸውን ተረፈ ምርቶች በተገቢው ቦታ ማስወገድ ግዴታው ነው፡፡

ከዚህ ውጭ የጋራ መጠቀሚዎችን (ኮሚናል ቤቶችን) በጋራ ይጠቀማሉ፡፡ የጋራ መጠቀሚ የሌላቸውን ደግሞ በዲዛይኑ የተመላከተ የጋራ መጠቀሚያ ካለ ባለው ቦታ ላይ ኅበረተሰቡም ተሳትፎ ቢሆን ሰርቶ መጠቀም ይችላል፡፡ ካሁን በፊት ያልተሰሩ ካሉ ግን መንግስት የሚሰራ ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ ጭፈራ ቤቶች አሉ፡፡ ይህም የድምጽ ብክለት ያመጣል፡፡ ይህን እንዴት ይመለከቱታል? በጋራ መኖሪያ ቤቶች ያሉ የንግድ ቤቶች ለምን ለምን ንግድ ስራ እንዲውሉ መመሪያችሁ ይፈቅዳል?**

**ኢንጂነር ስጦታው፡-** ኮንዶሚኒየም በተለይ 40/60ዎቹ እስከ ጂ+2 ያሉ ቤቶች የንግድ ቤቶች ናቸው። እነዚህ ቤቶች ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚሰሩት ለንግድ ተብሎ ነው፡፡ ቤቶቹ የሚተላለፉት በጨረታ ነው። ጨረታውን የሚያወጣው የቤቶች አስተዳደር ነው። ማንኛውም ሰው የንግድ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት መነገድ ይችላል፡፡ ነገር ግን የንግድ ስራዎች ሲሰሩ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማይረብሽ መልኩ መሆን አለበት፡፡ ነዋሪውን የሚረብሹ ነገሮች ካሉ የነዋሪዎች ኮሚቴ አለ እሱ እርምጃ ይወስዳል፡፡

ከዚህ ባለፈ ሳይቱ የሚገኝበት ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳም ተቆጣጥሮ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ከዚያ ባለፈ ግን ነጋዴዎች ይህን ነገድ ይህን አትነግድ ማለት አይቻልም፡፡ የንግድ ሕጉን ተከትሎ ሰው የፈለገውን መነገድ ይችላል፡፡ የተጫረቱት ቤት ስታንዳርዱን ካላሟላ የንግድ ፈቃድም አያገኙም። ለምሳሌ አንድ ሰው ክሊኒክ ልክፈት ቢል ፈቃዱን የሚሰጡት የጤና ተቋማት ናቸው፡፡ ስለዚህ ብቁ ካልሆነ እዚህ ተቋማት ፈቃዱን አይሰጡትም፡፡ በአጠቃላይ ንግድ ማካሄድ የሚፈቀደው የነዋሪውን ደህንነት እና ጤና ባገናዘበ መልኩ ብቻ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለልማት ተነሺዎች ኮንዶሚኒየም ቤቶች ይሰጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ቤት ለማግኘት የሚቆጥቡ ሰዎች ላይ ቅሬታ ይፈጥራል። በዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**ኢንጅነር ስጦታው ፡-** በልማት የሚነሱ ሰዎች ለከተማው ልማት ቤት እና ንብረታቸውን ይለቃሉ። እነዚህ ሰዎች ከቤታቸው ሲነሱ የግድ ማረፊያ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሚሰጡት ቤቶች ነዋሪው ከቆጠበው ቁጠባ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለልማት ተነሺዎች ነገም ዛሬም ቤቶችን እንሰጣለን፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ እድለኛ ያልሆኑ ሰዎች ቁልፍ ሰብረው እየኖሩ እንደሚገኙ ሰዎች ቅሬታ ያነሳሉ፡፡ ይህ ምን ያህል እውነታ ነው? እናንተስ ጉዳዩን ታውቁታላችሁ?**

**ኢንጅነር ስጦታው ፡-** በሕገ ወጥ ተያዙ የተባሉ ቤቶችን ትክክል ነው አግኝተናል፡፡ በየክፍለ ከተማው ካሉ የጸጥታ መዋቅሮች ጋር በመሆን ሕገ ወጦችን ከቤቶች እያስወጣ ነው፡፡ የተዘጋ ወይም ያልተላለፈ ቤት ሲያገኝ ሰብሮ ገብቶ የመቀመጥ ዝንባሌዎች አይተናል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕገወጦችን አስወጥተናል፡፡ አሁንም ክትትል እያደረግን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን ፡-ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**


**ኢንጂነር ስጦታው፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የገበያ ማዕከላቱን ለአርሶ አደሩና ለሸማቹ ተጠቃሚነት ምቹ የማድረግ ዝግጅት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት ገበያ ለማረጋጋት ጉልህ ሚና እንዳላቸው ታምኖባቸዋል፣

*መንግሥት እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማቃለል የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም እየሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም ከተሞች አምራች ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ የተለያዩ የምግብ ሸቀጦችን ከሚመረቱባቸው አካባቢዎች ወደ ከተማ በማምጣት ገበያን የማረጋጋት ሥራ ይሠራል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የማኅበረሰቡን የኑሮ ጫና ማቃለል ይችላሉ፤ ገበያን የማረጋጋት ሚናቸው ከፍተኛ ነው ያላቸውን በርካታ ሥራዎች ሲሰራ መቆየቱ ይታወቃል።*

ከተማ አስተዳደሩ ገበያን በማረጋጋት የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል እየሠራቸው ካሉ ተግባሮች መካከል የሰንበት ገበያ አንዱና ዋነኛው ሲሆን፤ በተለያየ ጊዜ የሚያዘጋጃቸው ባዛርና ኤግዚቢሽኖችም ገበያን በማረጋጋት የበኩላቸውን ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ወቅትም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ትላልቅ የገበያ ማዕከላትን በመገንባት አምራቹ ምርቱን በነጻነት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ወደ ገበያ ማዕከላቱ የሚያቀርብበትን፣ ሸማቹም ከዚህ ገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህም ገበያን በማረጋጋት የኑሮ ውድነት ጫናውን በማቃለል ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ታምኖበታል፡፡

በከተማዋ የመግቢያ በሮች አካባቢ የተገነቡት የግብርና ምርቶች ከዚህ አኳያ ይጠቀሳሉ፡፡ የገበያ ማዕከላቱ ገበያን በማረጋጋትና የኑሮ ውድነቱን በማቃለል ረገድ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ ናቸው፡፡ ዳይሬክተሩ፤ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ የገበያ ማዕከላቱ ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ወጪ መድቦ ያስገነባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ከተማ አስተዳደሩ የገበያ ማዕከላቱን ለመገንባት ከስድስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መድቧል፤ ይህንን ሲያደርግም የተለያዩ ግቦችን በማስቀመጥ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከልም አንደኛው የማኅበረሰቡን የኑሮ ውድነት ጫናን ማቃለል ሲሆን፤ ይህንን ለማስቻልም በገበያ ማዕከላቱ የሚቀርቡት ምርቶችን ሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚችልባቸውን አስቻይ ሁኔታዎች በማመቻቸት ነው፡፡

የገበያ ማዕከላቱ ከተገነቡ በኋላ ወደ ሥራ መግባት እንዲችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ቢሮው ባወጣው ግልጽ ጨረታ መሰረት ተወዳደሪዎች ተወዳድረዋል፤ አሸናፊ የሆኑ አካላትም ውል በመፈጸም የገበያ ማዕከላቱን መደብሮች ተረክበዋል። ጨረታውን ያሸነፉ የጅምላና ችርቻሮ ነጋዴዎች በገቡት ውል መሰረት የተለያዩ ምርቶችን ለከተማ ነዋሪው በተመጣጣኝ ዋጋ እንደሚቀርቡ አመላክተው፤ ይህም የኑሮ ውድነቱን ለማቃለልና ገበያውን ለማረጋጋት አበርክቶው የጎላ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ቢሮው በገበያ ማዕከላቱ ምርቶቻቸውን ማቅረብ ለሚችሉ የጅምላና የችርቻሮ ነጋዴዎች ግልጽ ጨረታ አውጥቶ ማወዳደሩን ጠቅሰው፣ ማንኛውም ነጋዴ ጨረታውን ተወዳድሮ ዕድሉን መጠቀም እንዲችል በተደረገው ጥረት በርካታ የጅምላና የችርቻሮ ነጋዴዎች ጨረታውን መወዳደር ችለዋል ብለዋል፡፡ ጨረታውን ከተወዳደሩት መካከል 57 የሚደርሱት የጅምላ ነጋዴዎች እንዲሁም 143 የሚደርሱት ደግሞ የችርቻሮ ነጋዴዎች ጨረታውን ማሸነፋቸውን ጠቅሰው፣ ነጋዴዎቹ በአሁኑ ወቅትም ምርቶቻቸውን ወደ ማዕከላቱ በማስገባት ወደ ሥራ እየገቡ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የገበያ ማዕከላቱ ዋና ዓላማ ገበያን በማረጋጋት የኑሮ ውድነቱን ማቃለል እንደመሆኑ በተለይም የጅምላ ነጋዴዎችን ለማወዳደር የተለያዩ መስፈርቶች መቀመጣቸውን ገልጸዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አንደኛ በኢንቨስትመንትም ሆነ በተለየ መንገድ መሬት ያለውና በተለያየ መንገድ የሚያመርት መሆን ይኖርበታል፤ ለዚህም ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ማቅረብ መቻል አለበት፡፡ ሁለተኛው መስፈርት በተሰማራበት ዘርፍ ዓመቱን ሙሉ ለከተማው ምርት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ሶስተኛው መስፈርት የሚያቀርባቸውን ምርቶች ከመደበኛው ገበያ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ ማድረግ የሚችል መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት የቻሉ 57 የጅምላ ነጋዴዎችና 143 የችርቻሮ ነጋዴዎች ወይም የንግድ ድርጅቶች አሸናፊ መሆን ችለዋል ነው ያሉት፡፡

በከተማዋ የመግቢያ በሮች አካባቢ የተገነቡት እነዚህ የገበያ ማዕከላት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙና የተለያየ አገልግሎት ያላቸው እንደሆኑ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ አንደኛው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኝና የሰብል ምርቶች የሚቀርቡበት የገበያ ማዕከል እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ሁለተኛው ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ሲሆን፣ ሶስተኛውም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የተገነባው የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ነው፡፡

ከተማ አስተዳደሩ እነዚህን የገበያ ማዕከላት ሲገነባ በዋነኛነት የኑሮ ጫናን ማቃለል ዓላማው እንደሆነ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ መሬት ያለውና አምራች የሆነ አካል በጨረታው እንዲሳተፍ መደረጉ በመሀል ያለውን ደላላ ከማስወጣት ባሻገር ጣልቃ ገብነትን ለመቀነስና የግብይት ሰንሰለቱን ለማሳጠር አበርክቶው የጎላ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡ ይህም የተለያዩ ምርቶች ከአምራቹ በቀጥታ ወደ ሸማቹ የሚደርሱበትን ዕድል እንደሚያመቻች አስታውቀዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ እነዚህ የገበያ ማዕከላት ሙሉ ለሙሉ ወደ ተግባር ሲገቡ የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር አላስፈላጊ የሆነ የደላላ ጣልቃ ገብነትን በማስወገድ ገበያን ለማረጋጋት ይረዳሉ። ምርትን በማጓጓዝና በክምችት ረገድ ይፈጠር የነበረውን የምርት ብክነት በመቀነስ ከፍተኛ የሆነ አበርክቶ ይኖራቸዋል፡፡ የገበያ ማዕከላቱ በተለይም አሁን ላይ በከተማው እየታየ ያለውን የኑሮ ውድነት ጫና ለማቃለል ትልቅ አቅምና ጉልበት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በየሳምንቱ የዋጋ ጥናት እንደሚያደርግ የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ በገበያ ማዕከላቱ የሚቀርቡት ምርቶች ከመደበኛ ገበያው ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ ማድረግ መቻል አለመቻላቸውን በሚያቀርበው ዋጋ መሰረት ክትትል እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡ ነጋዴዎቹ ዓመቱን በሙሉ ምርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ጠቅሰው፣ ይህም በውላቸው መሰረት የሚተገበር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ዓመቱን ሙሉ ምርታቸውን ለማቅረብ ውል መግባታቸውን ጠቅሰው፣ ይህንንም ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አመላክተዋል፡፡

እነዚህ ስምምነቶች በከተማ ውስጥ የሚታየውን የኑሮ ውድነት በማቃለል እንዲሁም ገበያን በማረጋጋት ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ተናግረው፤ የኑሮ ጫናው በተለይም በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ በሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማቃለል ትልቅ አቅም እንደሚፈጥሩ ያላቸውን ዕምነት አመልክተዋል፡፡

የገበያ ማዕከላቱ ያላቸው አበርክቶ ከፍተኛ እንደመሆኑ በፍጥነት ወደ ተግባር ገብተው የታለመላቸውን ግብ መምታት እንዲችሉ ቢሮው የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ጨረታውን ላሸነፉ አካላት ቢሮው ሱቆቹን እያስረከበ እንደሆነና ነጋዴዎቹም ወደ ሥራ እየገቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ነጋዴው ሱቁን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ የሱቅ ኪራይ የመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን ጭምር የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ጠቅሰው፣ በቶሎ ወደ ሥራ እንዲገቡ እንደሚደረግም ተናግረዋል፡፡

‹‹አዲስ አበባ ከተማ ሸማች እንጂ፤ አምራች ከተማ አይደለችም›› ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ቢሮው በተቻለ መጠን ከተማ ውስጥ ገበያው እንዲረጋጋና ኅብረተሰቡ ዕለት ዕለት የሚጠቀምበት ምርት ዋጋው እንዲቀንስ ለማድረግ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡ በከተማ ውስጥ ያለው የአብዛኛው ምርት ዋጋ ተገቢነት የሌለው ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ለዚህም ዋናው ምክንያቶቹ በገበያ ውስጥ የተለያዩ ጣልቃ ገብነቶች መኖራቸው ነው ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የአትክልት ምርቶች ዋጋ የመቀነስ አዝማሚያ እያሳየ መሆኑን አንስተው፤ በተለይም ሽንኩርት መጠነኛ ቅናሽ ማሳየቱንና ቲማቲምም እንዲሁ በከፍተኛ መጠን ቅናሽ እያሳየ መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል፡፡ ቢሮው ቲማቲምም ሆነ ሌሎች ምርቶች ዋጋቸው አሁን ካለው ዋጋ በታች ወርዶ ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ያለውን ፍላጎት ገልጸዋል፡፡ ይህ ማለት አርሶ አደሩ ይጎዳ ማለት እንዳልሆነና አርሶ አደሩ የልፋቱን ዋጋ አያግኝ ማለት እንዳልሆነ ተናግረው፣ አርሶ አደሩም የልፋቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ በኩል የገበያ ማዕከላቱ ጉልህ ሚና አላቸው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በገበያ ማዕከላቱ ምርቶቻቸውን ከሚያቀርቡት ነጋዴዎች መካከል አብዛኞቹ የአርሶ አደር ማኅበራት ናቸው፡፡ ከዚህ ቀደም አርሶ አደሩ ምርቶቹን ወደ ከተማ በማምጣት ለሸማቹ በቀጥታ የማቅረብ ዕድል አልነበረውም። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሶስትና አራት ደላሎች በመሀል ጣልቃ የሚገቡበት ሁኔታ ነው፡፡ አሁን ግን አርሶ አደሩ ምርቱን ካመረተበት ቦታ በቀጥታ ወደ ገበያ ማዕከሉ መጋዘኖች የሚያስገባበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ምርቱ ከአምራቹ በቀጥታ ወደ ሸማቹ ይተላለፋል፡፡ በዚህም በመጀመሪያ ደረጃ አርሶ አደሩን በተመሳሳይ መልኩም ሸማቹን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል ብለዋል፡፡

ይህ ለአርሶ አደሩና ለሸማቹ ጠቃሚ እንደሆነ የታመነበት የገበያ አማራጭ በዋናነት በመሀል ያሉትንና ምንም እሴት የማይጨምሩ ደላሎችን የሚያስወግድ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እነዚህ መሀል ላይ ያሉት አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶች ለብዙ ምርቶች ዋጋ መናር ብቸኛ ምክንያቶች ባይሆኑም ትልቅ ድርሻ አላቸው ብለዋል። እነዚህ ደላሎች አንዳንድ ጊዜ ወደ ከተማ የሚገባውን ምርት ዋጋና የምርት መጠኑን ጭምር የሚወስኑበት ሁኔታ እንዳለም ጠቅሰው፣ እነዚህን አካላት በአካል ማግኘት እንደማይቻልም ነው ያመላከቱት፡፡

በከተማዋ መግቢያ በሮች የተገነቡት የገበያ ማዕከላት እነዚህን እና መሰል የገበያ ችግሮችን ለማቃለል ትልቅ አቅም እንደሆኑ ያስታወቁት ዳይሬክተሩ፤ አርሶ አደሩንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ የገበያ ማዕከላት እንደሆኑ ገልጸዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ ምርቱን በቀጥታ ማቅረብ፣ ገበያውም ዋጋውን መወሰን የሚችልበት ዕድል ከተፈጠረ ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ እርግጥ ነው አሁን ያለው ሁኔታ አርሶ አደሩን ብዙም ተጠቃሚ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ወደ ከተማ ሲመጣ ደግሞ ሸማቹ ተጠቃሚ አይደለም፡ ፡ ይህ የሚሆነው መሀል ላይ ባለው ረጅም ሰንሰለት ሳቢያ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ማእከላት ይህንን የረዘመ የደላላ ሰንሰለት በማሳጠር ረገድ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

ግንባታቸው ተጠናቅቆ ወደ ተግባር ከተሸጋገሩት አራት የገበያ ማዕከላት በተጨማሪም ግንባታቸው ያልተጠናቀቁ ሌሎች የገበያ ማዕከላት በከተማዋ እየተገነቡ እንደሆነ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከተገነባው የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ጋር በተመሳሳይ ደረጃ የሚገነባ የገበያ ማዕከል ግንባታም እየተፋጠነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም እነዚህ የገበያ ማዕከላት ከዚህ ቀደም ተገንብተው ወደ ስራ ከገቡ የገበያ ማዕከላት ተሞክሮ በመውሰድ የታለመላቸውን ዓላማ ማሳካት እንዲችሉ ከማድረግም ባሻገር ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን ዕድል ለመፍጠር ጭምር ብርቱ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ዳይሬክተሩ አመላክተዋል፡፡

# የድምፅ ብክለት መፍትሔ ሲያገኝ ይሆን?

**ዋለልኝ አየለ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባለፈው ሳምንት ከአዲስ አበባ ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ውይይት አድርገው ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ ከተናገሩት አንዲት ነገር ቀልቤን ገዛችው፡፡ ለዓመታት ብሶቴን ስገልጽ የቆየሁበት ጉዳይ ነበር፡፡ በዚህ ጋዜጣ ላይ እንኳን በተደጋጋሚ ትዝብቴን ጽፌያለሁ፡፡ ጓደኞቼ እስከሚታዘቡኝ ድረስ ስለድምፅ ብክለት በተደጋጋሚ አማርራለሁ፡፡ ካፌ ወይም ሆቴል ስንመርጥ ከአገልግሎቱ ጥራት ይልቅ የፀጥታው ጉዳይ ያሳስበኛል፡፡ በሆነ አጋጣሚ አንድ ጩኸት የሌለበት ቤት ካወቅኩ ሁለት ታክሲ ይዤ ሁሉ ልሄድ እችላለሁ፡፡

የድምፅ ብክለት ነገር ያን ያህል አጀንዳ ሆኖ ሲወራበት አይሰማም፤ ዳሩ ግን አደገኛ ችግር ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማን ገጽታም የሚያበላሽ ነው፡፡ አጣዳፊ ሕመም ስላልሆነ ልብ አይባልም እንጂ የጤና ጠንቅ ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ከቤት ወጣ ከተባለ በየትኛውም አካባቢ ብዙ አይነት ጩኸት ያጋጥማል፡፡

ለዚህ ለጩኸት ባለኝ የመረረ ብሶት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለድምፅ ጩኸት አደገኛነት ሲያወሩ ሰማሁ። የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ ያሉ የድምፅ ከፍታዎች ለከተማዋም ለሰው ልጆች ጤናም ያላቸውን ስጋት ሲናገሩ፤ ችግሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድረስ ከታወቀ መፍትሔ ይደረግለት ይሆን? ብየ ጓጓሁ፡፡

ሁሉም ማለት ይቻላል አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ የድምፅ ብክለቶች በኋላቀርነትና በመሐይምነት የሚከሰቱ ናቸው። ከፊቱ ያሉ ተሽከርካሪዎች የትራፊክ መብራት ይዟቸው እያየ ያለምንም ማቋረጥ ጡሩንባውን የሚያንባርቅ አሽከርካሪ ብዙ ነው፡፡ በተለይም እንደ አውቶብስ ያሉ ትልልቅ ተሽከርካሪዎች ድምፃቸው እንዴት እንደሚረብሽ ማንም ያውቀዋል፡፡ «ሃይገር» የሚባለው ተሽከርካሪ «ክላክስ» ካደረገ ለደቂቃዎች ጆሯችን ይደነዝዛል፡፡

«ክላክስ» አያድርጉ ማለት አይደለም፡፡ የሚያናድደው ያለምንም ምክንያት ማድረጋቸው ነው፡፡ በእግረኛ መንገድ ላይ ለሚሄድ ሰው ሁሉ ሊያንባርቁ ይችላሉ፡፡ ጩኸታቸው እንዴት እንደሚሰቀጥጥ! አንዳንዶቹ የቤት ውስጥ ኑሯቸው ትዝ ሲላቸው ሁሉ ብስጭታቸውን በክላክስ የሚገልጹ ይመስለኛል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ዝም ብሎ ወፈፍ የሚያደርጋቸው ነገር አለ፡፡ አንድ ገጠመኝ ልናገር፡፡

አራት ኪሎ ከንብ ባንክ ሕንጻ ፊት ለፊት ያሉት ጁስ ቤቶች አጠገብ ነው፡፡ አንድ የቤት መኪና የያዘ ሰው ዳር አስይዞ ቆሟል፡፡ ቆሞ ግን በክላክስ አካባቢውን ያናውጣል፡፡ ሰዎች «ምን ሆኖ ነው?» በሚል ስሜት ዞር እያሉ ያዩታል፡፡ በረንዳ ላይ የተቀመጡት ደግሞ «ምናባቱ ነው!» እያሉ ቆጣ እያሉ እንደገና ወደ ጨዋታቸው ይመለሳሉ፡፡ በዚህ መሐል አንዲት የጁስ ቤቱ አስተናጋጅ ወጣች፡፡ ለካ በክላክስ አስተናጋጅ እየጠራ ነበር፡፡ ለዚያውም ቶሎ ሰምታ ባለመምጣቷ ለመቆጣት ሲሞክር ነበር፡፡

እስኪ አስቡት! ይህ ምን አይነት መሐይምነት ነው? አስፋልት ላይ ሆኖ አስተናጋጅ በክላክስ መጣራት ምን አይነት አራዳነት መሆኑ ነው? ያለማቋረጥ ሲጮህ በሚውል ክላክስ እሷን እየተጣራ መሆኑን በምን ታውቃለች? አካባቢው ተሽከርካሪ የማይኖርበት ቢሆን ብርቅ ስለሚሆን ዞር ሊባል ይችላል፡፡ መሐል አራት ኪሎ የእሱ ክላክስ ምን አይነት ምሥጢራዊ አስማት ኖሮት ነው ካፌ ውስጥ ያለ አስተናጋጅ የሚያስወጣ?

አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች ክላክስ የሚያደርጉት ያለምንም አስፈላጊነት ነው፡፡ አንዳንዶቹ በእግረኛ መንገድ ላይ ለሚሄድ ሰው ክላክስ ያደርጋሉ፣ አብዛኞቹ ግን መሄጃ አጥቶ ለቆመ ተሽከርካሪ ነው ክላክስ የሚያደርጉት፡፡ ከፊት ያለው ተሽከርካሪ የቆመው መሄድ ጠልቶ አይደለም፤ መሄድ ስላልቻለ ነው፡፡ ከኋላው እንኳን ክላክስ መድፍ እና ታንክ ቢተኮስ መብረር አይችልም! ይህ መሆኑ እየታወቀ ግን ያለምንም ማቋረጥ አካባቢውን እስከሚያናውጥ ድረስ ያስጮሃሉ፡፡

ሌላኛው አደገኛ ጩኸት ደግሞ የሞንታርቦ ነገር ነው። በተለይ የበዓል ሰሞን ልብ ብላችሁ ከሆነ ከውስጡ የሚወጣውን ድምፅ ለመስማት እስከሚያስቸግር ድረስ ያስጮሁታል፡፡ እስከመጨረሻው በመለቀቁ ምክንያት ምን ቃል እየተነገረ እንደሆነ አይሰማም፡፡ ስንጥርጥርጥር የሚል ድምፅ ነው የሚሰማው፡፡ በጎዳና ላይ እያለፉ ሁለትና ሦስት ፌርማታ አልፈው ሁሉ ይረብሻል፡፡

ይሄው የሞንታርቦ ጩኸት አንዳንድ ግሮሰሪዎችና ምግብ ቤቶች ውስጥ ይገኛል፡፡ ገና በማለዳው ጆሮ የሚበጥስ ዘፈን ይከፈታል፡፡ በዚያን ሰዓት ማንን ያዝናናል ብለው እንደሚያስቡ አይታወቅም፡፡ ለመንፈሳዊ ጽሞና የሚከፈት መዝሙር ራሱ የሚረብሽ ይሆናል፡፡ መዝሙር የሚከፈተው ለመንፈሳዊ ጽሞና ነው፡፡ ዳሩ ግን ማታ ለዘፈን በከፈቱት ሞንታርቦ ጠዋት ደግሞ መዝሙር ይከፍቱበታል፡፡ ሲጀመር ሃይማኖታዊ የምስጋና መዝሙር ስካር እና ዝሙት ሲካሄድበት ያደረ ቦታ ላይ ባይከፈት ጥሩ ነበር፡፡ ፈጣሪን ማመስገን ጊዜና ቦታ አይመርጥም ከተባለ ግን ውስጥ ለገቡ ሰዎች ሊሰማ በሚችል መጠን እንጂ አካባቢውን በሚያጥለቀልቅ ድምፅ መሆን የለበትም፡፡

ሙዚቃ፤ ለመደሰት ከሆነ ለሰስ ባለ ድምፅ ሲሰማ ነው ማጣጣም የሚቻለው፡፡ ለመጨፈር ከሆነ ደግሞ በማለዳ የሚጨፍር የለም! ታዲያ ገና በማለዳው የጆሮ ታምቡር የሚበጥስ ሙዚቃ የሚከፍቱት ለማን ይሆን?

እንዲህ የሚደረገው አብዛኞቹ በኋላቀር አመለካከት ውስጥ ስላሉ ነው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ዘመን ሙዚቃ ብርቅ ነበር፡፡ ብርቅ ያደረገው ሙዚቃ የሚሰማባቸው አማራጮች (ቴፕ፣ ቴሌቪዥን፣ ጂ ፓስ... የመሳሰሉት) ስላልነበሩ ነው፡፡ በሁሉ ሰው ዘንድ ተደራሽ አልነበረም። በዚያን ጊዜ የገጠር ከተማ ውስጥ ያሉ ጠጅ ቤቶችና ጠላ ቤቶች ሙዚቃ የሚከፍቱት ደንበኛ ለመሳብ ነበር። ሙዚቃ ለመስማት ብሎ የሚገባ ሰው ይኖራል፡፡ ይህ ቢያንስ ከአሥራ ምናምን ዓመታት በፊት በገጠር ከተሞች የነበረ ነው፡፡

ዛሬ ላይ (ለዚያውም አዲስ አበባ ውስጥ) ሙዚቃ የደንበኛ መሳቢያ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል? ግድለም! ሙዚቃ የጊዜና የቦታ ገደብ ስለሌለው በስልክ ከመስማት በትልቅ ስፒከር መስማት ያስደስታል፡፡ ያ የሚሆነው ግን ሙዚቃውን ማጣጣም በሚቻልበት የድምፅ መጠን ሲሆን እንጂ መሰማማት እስከሚከለክል ድረስ በማስጮህ አይደለም፡፡

ሌላው እና በድፍረት የማይነገረው ደግሞ የሃይማኖት ተቋማት ነገር ነው፡፡ አብዛኞቹ አማኞች ነገሩን የሚያዩት «እምነታችን ተነካ» በሚል ስሜት ነው፡፡ እኔ የምከተለው ሃይማኖት ሌሎች ሰዎችን የሚረብሽ መሆን የለበትም፡፡ ሰዎች ያለመረበሽ ሰዋዊ መብት አላቸው፡፡ «...ተቀበል!» እያሉ በሞንታርቦ የሚደረግ የኃይል ስብከት፣ በድምፅ ማጉያ የሚደረግ «የ.... ማሰሪያ» የሚል የማጭበርበሪያ ልመና፤ ሊከለከሉ የሚገባቸው ናቸው፡፡ የየሃይማኖቱ ተቋማት እነዚህን ነገሮች ሊያስቆሙ ይገባል፡፡ በጥቂት አጭበርባሪዎችና አላዋቂዎች ምክንያት የየሃይማኖቱ ስም በወቀሳ መነሳት የለበትም! «ኤጭ! እነዚህ ደግሞ ጀመሩ!» እየተባለ የእምነቱን ስም በምሬት የሚያስነሳ መሆን የለበትም!

በአጠቃላይ የእምነት ተቋማትን ጨምሮ፣ ተሽከርካሪዎች እና ንግድ ቤቶች የሚለቁትን አካባቢን የሚረብሽ የድምፅ ልቀት ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል!

# ዓለም አቀፍ

## ከፍተኛ ጫና የበዛባቸው የሄይቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን መልቀቃቸው ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ለሳምንታት የዘለቀውን ከፍተኛ ጫና እና በሀገሪቱ እየጨመረ ያለውን የከፋ ነውጥ ተከትሎ የሄይቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ኤሪየል ሄንሪ ከሥልጣን ለመልቀቅ መስማማታቸውን የካሪቢያን ሀገራት ቡድን ሊቀ መንበር አስታወቁ።

የቀጣናው መሪዎች በሄይቲ የፖለቲካ ሽግግር ላይ ለመምከር ሰኞ ዕለት በጃማይካ መገናኘታቸውንም ተከትሎ ነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥልጣን ለመልቀቅ መስማማታቸው የተነገረው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአሁኑ ወቅት በታጠቁ ቡድኖች ወደ ሀገራቸው እንዳይመለሱ በመከልከላቸው በፖርቶ ሪኮ ውስጥ ይገኛሉ።

ከቀድሞው የሄይቲ ፕሬዚዳንት ግድያ፣ ከአውሮፓውያኑ 2021 ጀምሮም ሀገሪቱን ሲመሩ ቆይተዋል።


በጃማይካ መዲና ኪንግስተን የተካሄደውንም ስብሰባ ተከትሎ የካሪቢያን ሀገራት ማኅበረሰብ ሊቀመንበር እና የጋያና ፕሬዚዳንት ኢርፋን አሊ እንደተናገሩ “የሽግግር ፕሬዚዳንት ምክር ቤት መቋቋም፣ ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሰየም እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥልጣን መልቀቃቸውን እናረጋግጣለን” ብለዋል።

በቅርብ ቀናት ውስጥ የታጠቁ ቡድኖች የሄይቲ መዲና ፖርቲ ኦ ፕሪንስን ጎዳናዎች በመቆጣጠር ያልተመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ከሥልጣን እንዲለቁ ጠይቀዋል።

የታጣቂ ቡድኖች ጥምረት በፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ጥቃት በመሰንዘር እንዲሁም ሁለቱን የሄይቲ ትላልቅ እስር ቤቶች መውረራቸውን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዓለም አቀፍ የፀጥታ ኃይል በሀገራቸው እንዲሰማራላቸው ውል ለመፈረም በኬንያ ተገኝተው ነበር።

ከኬንያ ሲመለሱም ጠቅላይ ሚኒስትሩን የጫነው አውሮፕላን በተከታታይ ጥቃት ባስተናገደው የሄይቲ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን እንዳያርፍ ተደረገ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ሄይቲ የመመለስ ፍላጎት እንዳላቸው ቢገልጹም ይህንን ለማድረግ የሀገሪቱ የፀጥታ ሁኔታ መሻሻል እንዳለበት በኪንግስተን ውይይት ላይ መነገሩን አሜሪካ



**ኤሪየል ሄንሪ፣**

አስታውቃለች።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለሚደገፈው እና ኬንያ ትመራዋለች ተብሎ ለሚጠበቅ 1 ሺህ አባላት ያሉት የፀጥታ ኃይል 100 ሚሊዮን ዶላር ይሰጣል ብለዋል።

አሜሪካ አጠቃላይ ለፀጥታ ኃይሉ 300 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ለሰብዓዊ እርዳታ 33 ሚሊዮን ዶላር እንደምትመድብ አስታውቃለች።

የካሪቢያን አገራት መሪዎች የሆነው የካሪኮም ቡድን፣ ከአሜሪካ እና ከሄይቲ ተወካዮች ጋር በመሆን በፖለቲካው የሽግግር ማዕቀፍ ላይ ተወያይተዋል።

በሄይቲ የሚቋቋመው የሽግግር ፕሬዚዳንታዊ ምክር ቤት ሁለት ታዛቢዎች እና ሰባት ድምፅ ሰጪ አባላት ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል የግሉ ሴክተር፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ተወካዮች፣ የጥምረት ተወካዮች እና አንድ የሃይማኖት መሪን ያካተተ እንደሚሆን ፕሬዚዳንት ዓሊ አስታውቀዋል።

ምክር ቤቱ “በፍጥነት” ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትርን የመሾም ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ምክር ቤቱ አገሪቱ በአውሮፓውያኑ 2026 ለምታደርገው ምርጫ መንገድ ይጠርጋል ተብሎ ይጠበቃል ።

ፕሬዚዳንት ጆቬኑል ሞይስ ከተገደሉ በኋላ ሥልጣን የተቆናጠጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ሄንሪ የፀጥታው ሁኔታ መሻሻል አለበት በሚል ምክንያት ምርጫውን በተደጋጋሚ አራዝመውታል።

## የቦይንግን ምስጢር ያጋለጠው ግለሰብ መኪናው ውስጥ ሞቶ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቦይንግ የተሰኘው አውሮፕላን አምራች ኩባንያ የቀድሞ ሠራተኛ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሞቶ ተገኝቷል።

የቀድሞው ሠራተኛው የድርጅቱን ምስጢር በማጋለጥ ይታወቅ ነበር። ጆን ባርኔት ለቦይንግ ፋብሪካ ለ32 ዓመታት የሠራ ሲሆን በአውሮፓውያኑ 2017 ነበር ጡረታ የወጣው።

ከመሞቱ በፊት ባሉት ቀናት ቦይንግ በተመሠረተበት ክስ ላይ ምስጢር አሾላኪ ሆኖ ቀርቦ ምስክርነቱን እየሰጠ ነበር።

ቦይንግ በቀድሞው ሠራተኛው ሞት የተሰማውን ኃዘን ገልጧል። የቻርልስተን ክፍለ-ግዛት ባለሥልጣናት የግለሰቡን መሞት ሰኞ ዕለት ለቢቢሲ አረጋግጠዋል።

ባለሥልጣናቱ ግለሰቡ የሞተው ቅዳሜ ዕለት “ራሱ ላይ ባደረሰው ጉዳት” ነው ብለው ፖሊስ ምርመራ መክፈቱን አሳውቀዋል። ባርኔት ለ32 ዓመታት ከሠራበት ድርጅት ጡረታ የወጣው በጤናው ምክንያት እንደሆነ ተገልጦ ነበር።

ከአውሮፓውያኑ 2010 ጀምሮ ኖርዝ ቻርልስተን በሚገኘው የድርጅቱ ማምረቻ ጣቢያ 787 ድሪምላይነር የተሰኘው ውድ



**ጆን ባርኔት፣**

አውሮፕላን ጥራት ተቆጣጣሪ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል።

በ2019 ባርኔት፤ ሠራተኞች ጫና እያደረባቸው ጥራታቸው የወረዱ ቁሳቁሶችን አውሮፕላኖች ላይ እየገጠሙ ነው ሲል ለቢቢሲ ተናግሮ ነበር።

ግለሰቡ አክሎ በተለይ በኦክስጅን መሣሪያዎቹ ላይ ችግር መኖሩን ጠቁሞ በአደጋ ጊዜ ከአራት የኦክስጅን ጭምብሎች አንዱ ላይሠራ ይችላል ሲል መረጃ አሾልኳል።

ጆን ባርኔት እንደሚለው ወደ ሳውዝ ካሮላይና የድርጅቱ ጣቢያ ከተዛወረ በኋላ አውሮፕላኖች ቶሎ እንዲደርሱ በሚል በፍጥነት ይመረቱ ነበር፤ ይህ ደግሞ ደኅንነታቸውን አደጋ ላይ ይጥለዋል። ቦይንግ ይህን ወቀሳ ፍፁም ሐሰት ነው ሲል ያስተባብላል።

ግለሰቡ ለቢቢሲ ጨምሮ እንደተናገረው ኩባንያው የሚገባውን መመሪያ እየተከተለ ስላልሆነ አንዳንድ ቁሳቁሶች ሳይገጠሙ እየተረሱ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ቁሳቁሶች ከቆሻሻ መጣያ እየተነሱ ተገጥመው አውሮፕላኑ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ይደረጋል ሲልም ተናግሮ ያውቃል።

ባርኔት ይህንን በተመለከተ ያለውን ስጋት ለአለቆቹ ቢያሳውቅም ምንም ዓይነት ምላሽ አለማግኘቱን ይናገራል።

የግለሰቡን ቅሬታ ቦይንግ ቢያስተባብለውም በ2017 የአሜሪካው አቪዬሽን ባለሥልጣን [ኤፍኤኤ] ባደረገው ምርመራ አንዳንድ የባርኔት ቅሬታዎች ውሀ ያነሳሉ ብሎ ነበር።

በተለይ የአንዳንድ ቁሳቁሶች ጥራት ማነስ እና የኦክስጅን ጭምብሎች ችግር ማስተዋሉን ያሳወቀው ባለሥልጣኑ ቦይንግ ይህን በፍጥነት እንዲያስተካክል ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ባርኔት ጡረታ ከወጣ በኋላ ከድርጅቱ ጋር ለረዥም ጊዜ የቆየ እሰጥ-አገባ ውስጥ ገብቶ ነበር። ባወጣሁት የደኅንነት ስጋት ምክንያት የሥራ ሕይወቴ እንዲበላሽ እንዲሁም ያልሆንኩትን እንደሆንኩ አድርጎኛል ሲል ድርጅቱን ቢከስም ቦይንግ ይህን ያስተባብላል።

ባርኔት በሞተበት ወቅት ወደ ቻርልሰተን ክፍለ ግዛት የመጣው ከዚህ ጋር በተያያዘ ላለበት የሕግ ሂደት ቃለ-ምልልስ ለመስጠት ነበር። ቅዳሜ ዕለት ለነበረው ቀጠሮ ሳይገኝ በመቅረቱ የት እንዳለ ሲጣራ ያረፈበት ሆቴል የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ ላይ መኪናው ውስጥ ሞቶ ተገኝቷል።

ቦይንግ እና የድርጅቱ አስፈላጊ ቁሳቁሶች አምራች የሆነው ስፒሪት ኤሮሲስተምስ በጥራት ምክንያት በርካታ ወቀሳ እየቀረበባቸው ይገኛል። ባለፈው ጥር አንድ አዲስ ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን ከፖርትላንድ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ከተነሳ ከደቂቃዎች በኋላ በሩ ተገንጥሎ መውደቁ ይታወሳል።

የአሜሪካ ትራንስፖርት ደኅንነት ጉዳዩን አጣርቶ አራት አስፈላጊ ብሎኖች በሥርዓቱ አልተገጠሙም ብሏል።

## ነፃ ሃሳብ

# ዛሬም በታላቅ ማንነታችን፣ በከበረውም ስማችን እንኑር!

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ፊት፣ ቀና ብላ በኩራት እንድትራመድ ካደረጓት ደማቅ ገድሎች መሀል አድዋ አንዱ ነው፡፡ አድዋ እውነት ከማይመስሉ ግን ደግሞ እውነት ከሆኑ የዓለም ታላላቅ ገድሎች ውስጥ አንዱ ለመሆን የበቃ እልህ አስጨራሽ የሕልውና ፍልሚያ የፈጠረው አንጸባራቂ ድል ነው፡፡ በሁለት ጎራ ባሉ (ራስወዳድና ፍትሀዊ ነፍሶች) መሀል የተደረገ የባሕል፣ የታሪክ፣ የማንነት፣ የነጻነት፣ የክብር፣ የሉአላዊነት ተጋድሎ ነው፡፡

አንዱ በኃይል ሌላው በሕዝባዊነት ሉአላዊነታቸውን ለማስቀጠል ያደረጉት የማንነት ትንቅንቅ በስተመጨረሻም ሕዝባዊነትን ይዘው ለፍትህ በቆሙት ነፍሶች የበላይነት ተጠናቀቀ፡፡ እንደ አድዋ ያሉ ለሰው ልጅ ሁሉ ትንሳኤ በመሆን በዘመን ውስጥ ሳይንገዳገዱ ማለፍ የሚችሉ የታሪክ አንጓዎች እንዴት ተከሰቱ ብለን ስንጠይቅ፣ ከዘርፈ ብዙ ምክንያቶቹ ውስጥ በቀዳሚነት የምናገኘው ሕዝባዊነትን ነው፡፡

ሕዝባዊነት ከድልና እድል ባለፈ በትውልድ እና በታሪክ መሀል የሚቀመጥ የብዙሀነት ቀለም ነው፡፡ አድዋን ማን ፈጠረው? እንዴት ተፈጠረ? አላማውና አስተማሪነቱስ ምንድነው? ብለን ብንጠይቅ እኚህን መልሶች በቀዳሚነት እናገኛለን፡፡ እናም አድዋን ማን ፈጠረው? ከሚለው ጥያቄ ብንጀምር አንድነትና ሕዝባዊነት ባበሩበት የፍትህና የሚዛናዊነት እሳቤ በኩል ተፈጠረ የሚል መልስን እናገኛለን፡፡

በግርድፉ ብንናገር የኢትዮጵያውያን የድል ብስራትን እንመለከታለን፡፡ ኢትዮጵያውያን ዝም ብለው ወደ ጦርነት አልገቡም፡፡ በተቻላቸው ሁሉ በፍቅርና በንግግር ለመፍታት ጥረት አድርገው ነበር።እብሪተኛው የጣሊያን ወራሪ ግን ይሄን የእንነጋገር ሀሳብ ሳይቀበል በአሸንፋለው መንፈስ ወደጦርነት ገባ፡፡ ሆኖም ግን እንዳሰበው የሆነ አልነበረም፡፡ ነጭ ለምንግዜም የሚያፍርበትን፣ ጥቁር ለሁልግዜም የሚኮራበትን የነጻነትና የእኩልነት ታሪክ ጽፈን አለፍን፡፡

ይሄ የታሪክ ምዕራፍ ገናናነት እንዴት ተፈጠረ? የሚለው ጥያቄ ማን ፈጠረው? በሚለው ስነልቦና የሚመለስ ነው፡፡ እንዴት ተፈጠረ የሚለው ጥያቄ በውስጡ ኢትዮጵያዊነትን ያቀለመ ሀሳብ ነው፡፡ አድዋ እንዴት ተፈጠረ? የሚለውን ጥያቄ “በሀሳብ በላቁ፣ በአንድነት በበረቱ፣ ስለሉአላዊነታቸው እንቅልፍ በማይተኙ ነፍሶች ተፈጠረ” ብለን መመለስ እንችላለን፡፡

አላማውና አስተምህሮቱ ለዚህኛውም ሆነ ለዛኛው ትውልድ አንድ አይነት መልክ ያለው ነው። የአድዋ መነሻ በክተት አዋጁ ላይ እንደተጠቀሰው ሀገርና ርስትን ሊቀማ የመጣ፣ ባህልን ሊበርዝ፣ ማንነትን ሊቀይጥ የመጣ ባዕድ እንደሆነ ይታወቃል። ይሄን መነሻ አድርገን ብንናገር የእኛ የተጋድሎ ዓላማና የአድዋ ውጤት መድረሻ ኢትዮጵያዊነትን መታደግ፣ ታሪክና ባሕልን ማስቀጠል፣ ነጻነትንና ሉዓላዊነትን ትርጉም መስጠት ከምንም በላይ ደግሞ አብሮነትንና ወንድማማችነትን ማስቀጠል እንደሆነ እንረዳለን፡፡

አድዋ ብለው የተናገሩ የትኛዎቹም ጠቢብ አፎች፣ አድዋ ብለው የጻፉ የትኛዎቹም በሳል ብዕሮች ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ መነሻቸውን ሀገር መድረሻቸው ሕዝብ አድርገው ነው፡፡ መነሻና መድረሻው ሀገርና ሕዝብ የሆነ አእምሮና ልብ የአባቶቹን መንፈስ ወርሶ አንዲት ሀገርን ይፈጥራል እንጂ በታሪክ ተወቃሽ ለመሆን የአድዋን የአብሮነት መልክ አያደበዝዝም። አድዋ ከእኛ አልፎ አፍሪካ፣ ከዛም ዓለም አቀፍ የሆነ የአስተሳሰብ፣ የርዮተዓለምና የጥቁርነት ገናና ማህተም ነው፡፡ በዚህ ማህተም ካላማርንና ካልደመቅን፣ ካልሻርንና ካልታከምን፣ ካልተቃቀፍንና ካላበርን ሌላ የኢትዮጵያዊነት ቀለም የለንም፡፡

አድዋ ኢትዮጵያዊነት የተሰበሰቡበት፣ የተሳሰ ቡበት፣ የተለቁበት፣ የተደማመጡበት፣ የመከሩበትና የተዋሃዱበት የታሪክ ዋርካ ነው፡፡ በዚህ ዋርካ ስር እኔነትና ዘረኝነት አልነበረም፡፡ ብሄርና ጎሳ፣ ዘርና ቋንቋ አልነጣጠሏቸውም፡፡ ጥላቻና መገፋፋት፣ ቂምና ቅራኔ አጥር አልሰሩም፡፡ እናም የዓድዋ ዋርካነት ሁሉንም በእኩል ያስጠለለ የእውነተኛይቱ የኢትዮጵ ስም ነበር፡፡ ይሄ ስም ለመላው ዓለም የነጻነት ብርሀንን ፈንጥቆ መላውን የሰው ልጅ ነጻ ያወጣ የጥቁርነት የጽናት ተምሳሌት ነው፡፡

በአድዋ የአንድነት ዋርካ ስር ኢትዮጵያዊነት ለምልሞ ነጻነት መጥቷል፡፡ የዘመናት የነጭ የበላይነት ተሽሮ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል መሆኑ እንደአዲስ የምስራች ተበስሯል፡፡ ከአድዋ ድል በኋላ ዓለምና ሕዝቦቿ በተለይም ነጮቹ ከነበሩበት የኃይልና የአንባገነንነት እሳቤ ወጥተው እኩልነትና ሰብዐዊነት ያለበትን አዲስ የሕይወት ልምምድን እንዲለማመዱ ሆነዋል፡፡

ባርነትና ጭቆና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሽረው ሰብዐዊነት የነገሰበት ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰው የሚሉት ፍጡር ከዘርና ከቀለም ርቆ በፍትህና በእኩልነት ሚዛን ብቻ እንዲለካ አስገዳጅ ስርዐትም ሰፍኖ ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ አዲስ ስርዐት ከአድዋ በኋላ በኢትዮጵያውያን የተፈጠረ የብዙሀን ከእስራት ነጻ የመሆን የከእንደገና መወለድ ቀን ነበር፡፡

ለራስ ተርፎና በቅቶ ሌሎችን የነጻ ፋና መሆን ደስ ይላል፡፡ የነጻነት ምልክትነት በውስጡ በርካታ ሕብረብሄራዊ መልኮች ያሉት ማንነት ነው፡፡ አንድ ሀገር የነጻነት ምልክት ነው የሚባለው ለራሱ በቅቶ ራሱን ሲችል ነው፡፡ እኚህ ሂደቶች ደግሞ ብዙ መመዘኛዎች አሉት፡፡ ሌሎች ያልቻሉትን ችለን አፍሪካንና መላው ዓለምን ከባርነት ነጻ ስናወጣ አውቀንና ተረድተን፣ ተግባብተንና ተዋህደን፣ ተስማምተንና አብረን ቆመን ነው፡፡

እኚህ ውህደቶች ደግሞ ዝም ብለው አይመጡም ከታሪክና ከማንነት ጋር የተዋረሱ ሆነው የሚጠሩ ናቸው፡፡ ለሶስት ሺ ዘመን በሀገርነት ስንጠራ ምን ነበርን፣ እንዴት ነበር ሀገርና ሕዝብ የሆነው የሚለው ጥያቄ ይሄን ማንነታችንን የሚናገር እውነታ ነው። ከጥንት እስከዛሬ ብዙዎችን ከባርነት፣ ከጭቆና ነጻ እንዲወጡ መንገድ አሳይተናል፡፡ ለብዙ ሀገራት የሰላምና የመረጋጋት አስተዋጽኦ አድርገናል። ብዙዎች እንደሀገር እንዲቀጥሉ ከተሞክሯችን አካፍለናል፡፡ በዲፕሎማሲውና በመልካም ግንኙነት የራቀ ታሪክ አለን፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ አድዋ ተፈጠረ፡፡ እናም የነጻነት ፋናዎች ተባልን፡፡

የተጀመረው እንዲቀጥል፣ የቀጠለው ፍሬ እንዲያፈራ በአባቶቻችን የነጻነት መንፈስ መቀጠል አማራጭ የሌለው ግዴታችን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በአንድነት የደመቀው የድሮው አድዋዊ ስማችን ዛሬ ላይ በእኔነትና በራስወዳድነት ጨቅይቶ ክፍተት እያበጀ ነው፡፡ አሁናዊው የአንድነት መንፈሳችን መሸርሸር ነው ዛሬ ላይ ብሄር ወለድ ቁርሾዎች እንዲበረክቱ ያደረገው፡፡

እዚህጋ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ፣ አንዳንድ ነገሮች ቀላል ይመስላሉ ግን ለትላልቅ ውድቀት መንገድ የሚጠርጉ ናቸው፡፡ ታላላቅ የሰውነት ስብራቶች ቀላል በሚመስሉ ነገሮች በኩል የመጡ ናቸው፡፡ እንደ ሀገር የምንሰቃይባቸው የብሄር አስተሳሰቦችም በነዚህ በኩል ሰርገው የገቡ ስለመሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ ለትናንሽ ነገሮች መንገድ ስንዘጋ ትላልቅ ሁነቶች እንዲቀጥሉ እድል እንሰጣለን፡፡ አድዋና መንፈሱ በዚህ ትውልድ ላይ እንዲደገም እነዚህ ትንሽ የሚመስሉ የልዩነት አስተሳሰቦች መደብዘዝ አለባቸው፡፡ ከብዙሀን የተሰጠን የነጻነት ዓርኣያነት ስም እንዲቀጥል በትንንሽ ሀሳብ መቧደናችንን ትተን ሀገር በሚጠቅም ትልልቅ ሀሳብ ስር መውደቅ አለብን፡፡

አድዋ የትልቅ ሀሳብ ውጤት ነው፡፡ በእኛ ትልቅ ሀሳብ በኩል የተንጸባረቀ የብዙሀን የትንሳኤ ጮራ ነው። በመሳፍንቶች መሀል ያሉ ትንንሽ አለመግባባቶች ተዘግተው ስለኢትዮጵያ በአንድነት የተከፈለ መስዋዕት ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ ተነስተን አድዋንና የዛን ዘመን አስተሳሰብ ብንዳስስ በመሳፍንቶች መሀል የነበረው አለመግባባትና ቅሬት ከሀገር የማይበልጥ ትንሽ ሀሳብ መሆኑን እንደርስበታለን፡፡ እነዛን ትናንሽ ውስጣዊ ችግሮች ትተን ስለሀገር ስለተቧደንን ነው አድዋን የፈጠርነው። ከሀገራችን ቅሬታዎቻችን በልጠው ቢሆንና ለቅሬታዎቻችን ቅድሚያ ብንሰጥ ኖሮ አድዋን ውሀ አይኖርም ነበር፡፡

> አድዋ መነሻው ነጻነት፣ መድረሻው ደግሞ ሰብዐዊነት ነው፡፡ እኚህ ጥንድ የማንነት ደማቅ መልኮች ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ካልሆኑ የትም የሉም፡፡ ማንም በሌለው ክብር ውስጥ የቆምነው ማንንም በማይመስሉ አባቶቻችን ነው፡፡ በምን ኃይል፣ በምን ጥበብ፣ በምንስ ብቃት ነጭ በጥቁር ተሸነፈ ብለን ብናስብ ማረፊያችን የሚሆነው ኢትዮጵያዊነት የሚለው ሕብረ ውህድ ትልቅ ስም ነው

ይሄ እውነታ ለዚህኛውም ትውልድ የሚሰራ ነው። በዚህኛው ትውልድ ስር መንገድ ያልተዘጋባቸው ለትልቁ ሕዝባዊ ጉዳይ መንገድ የከለከሉ ጥቃቅን ሀሳቦች እዚም እዛም አሉ፡፡ በትርክት ተደናግረን ሀገር ለሚጠቅሙ፣ ትውልድ ለሚያሻግሩ ጠቃሚ ጉዳዮች ኋለኞች ሆነን የቆምን አለን፡፡ የማይጠቅሙንን ሸረን ለሚጠቅሙን ስንደክም ብቻ ነው ዳግማዊ አድዋን የምንፈጥረው፡፡ መንገድ ያልዘጋንባቸው ትናንሽ ሀሳቦች ትልቁን ሀሳብ ሸረው ዋጋ እያስከፈሉን እንደሆነ ሊገባን ይገባል፡፡

አሁን ላለው ትውልድ ዳግማዊ አድዋን መፍጠሪያ ቁልፉ ተነጋግሮ መግባባት፣ ተግባብቶ አብሮ መኖር ነው፡፡ በእርቅና በምክክር ተጽዕኖ ፈጣሪነታችንን ማስቀጠል ከቻልን ያኔ የእኛ አድዋ ነፍስ ይዘራል፡፡ በመሀከላችን ገብተው ላደበዘዙን ትርክቶችና አፍራሽ አስተሳሰቦች ሁነኛ መልስ ስንሰጥ ያኔ ነጻ አውጪ ስማችን ይመለሳል፡፡ ጥበብ የትም አለ፤ ሆኖም እንደሚነጋገርና እንደሚወያይ ማኅበረሰብ ግን ጥበብ መልህቁን የጣለበት ስፍራ የለም፡፡ የሀሳብ ልዩነት መቼም ይኖራል፣ በምክክር አቃንቶና አስተካክሎ ለሀገር የሚበጅ ማድረግ ግን የዚህ ዘመን ቀዳማይ የቤት ስራው ሊሆን የሚገባ ነው፡፡

ታላላቅ ማኅበራዊ ተጽዕኖዎች ከመደማመጥ እንደሚመጡ የገባኝን ያክል ምንም ገብቶኝ አያውቅም፡፡ አለመደማመጥ ከፍ ሲልም ተነጋግሮ አለመግባባት ያኛውንም ይሄኛውንም አድዋ የሚሰውር ተግዳሮት ነው፡፡ የአባቶቻችን አድዋ አንድ ሁለተኛው የመደማመጥ ውጤት ነው፡፡ የእኛም አድዋ በመደማመጥ እንደሚጀምር ስናገር ከልቤ ነው፡፡ ያኛው ትውልድ በአንድነትና በወዳጅነት ተሳስሮ ኢትዮጵያዊነትን ሳያስነካ ከትውልድ ትውልድ አሻግሯል፡፡ ይሄኛው ትውልድም በተመሳሳይ አንድነቱን አስጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ አድዋ ትርጉም ያለው የሚሆነው የአባቶቻችንን መንፈስ ተቀብለን በአባቶቻችን መንፈስ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ስንችል ነው፡፡

በተለይ አሁን ላለነው ለእኛ የአድዋ መንፈስ ከምንም በላይ ያስፈልገናል፡፡ በኢትዮጵያዊነት መሀል የተሰገሰጉና ለመከፋፈል እድል እየፈጠሩ ያሉ ወይባ መልኮችን ለማጽዳትና ለማከም አድዋ መነሻችን መሆን ይችላል፡፡ ሕብረታችንን ለማጠንከር፣ አንድነታችንን አስቀጥለን ለመጓዝ አድዋን የፈጠረ የአባቶቻችንን መንፈስ እንደወኔና እንደመንደርደሪያ ልንጠቀመው ይገባል፡፡ ያለፉ የታሪክ ዳናዎቻችን ለሚደነቃቀፍ ማንነታችን ሁነኛ መማሪያ ነው። ካለፈው ተምረን መጪውን የተሻለ ማድረግ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ የጋራ ጉዳያችን ነው፡፡

አድዋ መነሻው ነጻነት፣ መድረሻው ደግሞ ሰብዐዊነት ነው፡፡ እኚህ ጥንድ የማንነት ደማቅ መልኮች ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ካልሆኑ የትም የሉም። ማንም በሌለው ክብር ውስጥ የቆምነው ማንንም በማይመስሉ አባቶቻችን ነው፡፡ በምን ኃይል፣ በምን ጥበብ፣ በምንስ ብቃት ነጭ በጥቁር ተሸነፈ ብለን ብናስብ ማረፊያችን የሚሆነው ኢትዮጵያዊነት የሚለው ሕብረ ውህድ ትልቅ ስም ነው፡፡

የጥቁሮች የአይበገሬነት በትር ያረፈበት የጣሊያን ጦር ተበታትኖና ፈርጥጦ ወደሀገሩ ሲመለስ የወቅቱ የጣሊያን ንጉስ አማኑኤል ኡምቤርቶ የልደት ቀን በመላ ሀገሪቱ የሀዘን ቀን እንዲሆን ያስገደደ የታሪክ ጀብዱ ነበር፡፡ ዋና ከተማዋን ሮምን ጨምሮ የጥቁሮቹን ንጉስ ስም በመጥራት “ምኒሊክ ለዘላለም ይኑር” በሚሉ ቁጣ በወለዳቸው ሕዝባዊ መፈክሮች እንዲጥለቀለቅም ምክንያት ሆኗል፡፡ እኚህ ሁሉ እውነታዎች አፈ ታሪክ ሳይሆኑ ከአድዋ ድል በኋላ የተከሰቱ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬም ይሄን መሰል ገናን ታሪክ ለመከተብ እንድንችል በትናንቱ ማንነትና ስማችን ከፍታ ልክ መገኘትን የግድ የሚለን፡፡

# ባለውለታዎቻችን

# የኢትዮጵያ እግርኳስ ባለውለታ

**ክብረአብ በላቸው**

የአፍሪካ እግር ኳስ ዋንጫ ሲታወስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ቀድመው ከሚታወሱ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ባለውለተኞች መካከል ስሙ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጨዋችና አሠልጣኝ እንዲሁም የሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ባለድሉ ብሔራዊ ቡድን አምበል ሉቺያኖ ቫሳሎ።

ትውልዱ በኤርትራ በ1927 ዓ.ም. እንደሆነ የሚነገርለት ሉቺያኖ ቫሳሎ፣ ሉቺያኖና ወንድሙ ኢታሎ ቫሳሎ ትውልድ የማይረሳቸው የዘመን ጀግኖችና፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ሁሌም ከፊት የሚያስቀድማቸው በታሪካዊ ውለታቸው አይረሴ የሆኑ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ባለውለታዎች ናቸው።

በእግር ኳስ ሕይወቱ ቀድሞ ድሬዳዋ ጥጥ ማኅበር (ወደ ኋላ ላይ ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ) እንዲሁም ለቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ በመጫወት ይታወቃል፡፡ በዘመኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተጨዋች ሆኖ ባደረጋቸው በተለያዩ የአፍሪካ ዋንጫዎች ላይ ኢትዮጵያን በመወከል፣ ከቡድኑ ጋር ታሪካዊ ተብሎ እስካሁን የሚጠቀሰውን ሦስተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ለኢትዮጵያ ከፍ ያደረገ ድንቅ እግር ኳስ ተጨዋች እንደነበርም የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

በ1954 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በተደረገው የ3ኛ አፍሪካ ዋንጫ ፍጻሜ ግብፅን 4 ለ2 ኢትዮጵያ ስታሸንፍ ወሳኝ ግብ ያስቆጠረው ሉቺያኖ ቫሳሎ፣ እግር ኳስ እንዲህ እንደ አሁኑ ባልዘመነበት በዚያን ዘመን ከተጨዋችነት ሕይወቱ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን በማሠልጠን ታሪክ የሚያስታውሰው ድንቅ ባለሙያ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ብቸኛው እና ትልቁ ድል ሲገኝ የቡድኑ መሪ በኤርትራ የተወለደው፣ ባለ ቅይጥ ዜግነቱ፣ በጣሊያንኛ ስም የሚጠራው የያኔው ታላቁ ተጫዋች ሉቺያኖ ቫሳሎ ነበር፡፡ ሉቺያኖ የተወለደው ከጣሊያናዊ የቱስካን ወታደር አባት ቪቶሪዮ ቫሳሎ እና ከኤርትራዊት እናቱ መብራቅ አብርሃም ነበር።

ከምንም ነገር ቀልድና ጨዋታ በመፍጠር የሚታወቀው ሉቺያኖ በአስመራ ጭርንቁስ መንደሮች እግርኳስን መጫወት ጀመረ፡፡ በአርነት ወይም (ነፃነት) ጎዳና ለሲኒማ ኢምፔሮ ቅርብ የሆነውና በአስመራ ከሚገኙ ኃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች አንዱ የነበረው ኮሌጂዮ ላቬላ የሉቺያኖ የእግርኳስ ህይወት በጥሩ ሁኔታ እንዲጀምር መንገድ ከፍቷል፡፡ ይህ የካቶሊክ ካቴድራል ትምህርት ቤት ስቴላ አስመሪና (የአስመራ ኮከብ) ተብሎ የሚጠራ የእግርኳስ ቡድን ነበረው፡፡

ጥቁርና ነጩ የቡድኑ መለያ በጣልያን- ኤርትራዊ (ኢታሎ-ኤርትራ) ጥንድ-ማንነት ላይ የተመሠረተው ቡድን መገለጫ ሆነ፡፡ በወቅቱ ክለቡ የተቋቋመበት ዋነኛ ምክንያት የቤተክርስቲያኗ አስተዳደሮች በከተማዋ በሚኖሩ ክልስ ታዳጊዎች አዕምሮ ውስጥ የሰፈነውን አሉታዊ የስነ-ልቦና ተጽዕኖ ለማስወገድ እንዲያስችል ታስቦ ነበር፡፡ በጊዜው ከጣልያናውያን አባቶች የሚወለዱ ልጆች በአባቶቻቸው ያለመፈለግ ችግር ይገጥማቸዋል። በኤርትራውያኑ ዘንድም ቢሆን የጨቋኙና ቅኝ ገዢው ዘር በመሆናቸው የመገለል እና የመነጠል ጫና ይደርስባቸዋል፡፡

ሉቺያኖ በስቴላ አስመሪና በግራ መስመር ተከላካይነት መጫወት ቢጀምርም ከቡድኑ ጋር ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ቆይታ አላደረገም፡፡ የእግርኳስ ክለቡ የተጫዋቹን ፍላጎት ማሟላት አልቻለም፡፡ ሉቺያኖም የሌሎች ክለቦችን ትኩረት አገኘ፡፡ የአገሪቱ የምድር ባቡር ሰራተኞች ጠርተው አወያዩት፡፡ ግሩፖ ስፖርቲቮ ፌሮቬሪ በኤርትራ የባቡር ድርጅት ክለብ ነበር፡፡ ድርጅቱ በባቡር መንገድ ጥገና ሰራተኛነትና በተጫዋችነት ሉቺያኖን ለመቅጠር ቢደራደርም የተጫዋቹ ልብ ግን ወደ ሰማያዊ ለባሾቹ ገጀረት አደላ፡፡

በከፍተኛ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ያለፉ የኤርትራ ተወላጆችን የያዘው ይህ ቡድን የሉቺያኖ ማረፊያ ሆነ። የቡድኑ አባላት በከፍተኛ አንድነትና ጠንካራ የቡድን መንፈስ የተሳሰሩ ነበሩ፡፡ የተለያዩ የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችን በመጠቀምና በየሳምንቱ መጠነኛ መዋጮ በማሰባሰብ የቡድኑን የበጀት እጥረት ለመቀነስ ይጥሩ ነበር፡፡

ሉቺያኖ በገጀረት እ.ኤ.አ ከ1953 ዓ.ም -1958 ዓ.ም ባሳለፈው የስድስት ዓመታት ቆይታ ቡድኑ ወደ ከፍተኛው የሊግ እርከን እንዲያድግ አይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ወደ ከፍተኛው ዲቪዚዮን ባለፉበት ዓመትም ገጀረት ከጣልያን ቡድኖች አንዱ በነበረው ግሩፖ ስፖርቲቭ ቪስቲኒቲ ላይ የተቀዳጀው የ 4-0 ድል የሉቺያኖን የላቀ ችሎታ ያሳየ ነበር፡፡ በጨዋታው ሉቺያኖ ያሳየው ብቃት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለመጫወት ያስቻለውን የመጀመሪያ ጥሪ አስገኘለት፡፡



የሉቺያኖ ቀጣይ ማረፍያ ግሩፖ ስፖርቲቮ ነበር። ይህ ቡድን አስመራ በአሰልጣኝ ኤንዞ አርቺዮሊ አማካኝነት ሶስት የሊግ ዋንጫዎችን እ.አ.አ. በ1945፣ በ1947 እና በ1948 ማሸነፍ ቻለ ነው፡፡ ሉቺያኖ ወደዚህ ክለብ በገባበት ጊዜ ቡድኑን በአምበልነት የሚመራው በአስመራ የሚገኙ የጣልያን ስፖርተኞች ምልክት የነበረው እና 'ኤርትራዊው ሄሬራ' በመባል የሚታወቀው ማሲሞ ፌኒሊ ነበር ፡፡ ፌኒሊ በጣሊያን እንደተወለደ ቤተሰቦቹ ይዘውት ወደ አስመራ መጡ፡፡ ጣልያናዊው ተጫዋች እ.ኤ.አ. እስከ 1974 ዓ.ም በነበረው የኤርትራ ቆይታው በአገሪቱ እግርኳስ ላይ ትልቁን አሻራ ያሳረፈ ሰው መሆን ችሏል፡፡

ቀጣዩ የሉቺያኖ የክለብ ዝውውር በክልስነቱ የሚፈጠርበትን አሉታዊ ተጽዕኖ በጉልህ ያመላከተ ነው፡፡ በ1950ዎቹ መጨረሻ ግሩፖ ስፖርቲቮ አስመራ የተባለው የጣልያኖች ቡድን ለሉቺያኖ የኮንትራት ጥያቄ አቀረበለት፡፡ የወቅቱ የክለቡ ፕሬዚዳንት ሰርጂዮ ሴሬኖ ወርሀዊ 600 የኢትዮጵያ ብር ደመወዝ እና በጣሊያኖቹ በሚተዳደረው የባቡር ትራንስፖርት ከፍተኛ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ውስጥ በመደበኛ ስራ የመቀጠር እድል አመቻቹለት፡፡ ለተጫዋቹ የቀረበለት ይህ ግብዣ እምቢ የሚለው አልነበረም፡፡ እናቱን እንዲሁም ሁለቱን ታናናሽ ወንድምና እህቱን (ኢታሎ እና ሊና) የሚረዳበትን አጋጣሚ ፈጠረለት። ይህን መጠሪያ ያገኘውም ታዋቂው ጣልያናዊ ስራ ፈጣሪ (ኢንተርፕረነር) ፍራንቼስኮ ሲሴሮና በዘመኑ በፋሽስቶች ከሚመሩት የእግርኳስ ቡድኖች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ክለብ በጋራ የማጠናከር ስምምነትን ከፈጠሩ በኋላ ነው፡፡

የአድዋው ሽንፈት በተለይ በጣሊያን ከፍተኛ ውዝግብን ፈጥሯል፡፡ በሽንፈቱ ምክንያት በአገሪቱ የነበሩት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተዘግተው የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክሪስፒም ከስልጣን ራሳቸውን አገለሉ፡፡ አዲሱ የስታዲየሙ ስያሜም እ.ኤ.አ. በ1962 በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ለተፈጠረው የመዋሀድ ውሳኔ መንገድ አመቻቸ። እ.ኤ.አ. በ1953 የኤርትራ የእግርኳስ ሻምፒዮና ከኢትዮጵያ የእግርኳስ ውድድር ጋር ተቀላቀለ፡፡ ከኤርትራ ሦስት ቡድኖች፣ ከሸዋ ክፍለ ሀገር እና ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ሌሎች አምስት ቡድኖች ተውጣጥተው የ8-ክለቦች ሻምፒዮና ተጀመረ፡፡

በወቅቱ በኤርትራ ይኖር የነበረው 1.5 ሚሊየን ሕዝብ ከ23 ሚሊየኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንፃር ሲታይ አነስተኛ መጠን የነበረው ቢሆንም ኤርትራውያኖቹ ከጣሊያን ባገኙት ልምድ የስፖርት ባህላቸው ከኢትዮጵያ የተሻለ ደረጃ ነበረው፡፡ ያኔ የኤርትራ ቡድኖች በተለያዩ ውድድሮች ይሳተፉ ነበር፡፡ ይህ "ፕሮፖጋንዳ" የሚል ስያሜ የነበረው ውድድር በተለያዩ



የኤርትራ ክፍሎች ወዲያው ተስፋፋ፡፡

እ.ኤ.አ በ1940ዎቹ የኤርትራ ቡድኖች ከጣልያኖቹ ጋር በመቀላቀል በሻምፒዮናው መሳተፍ ጀምረው ነበር። ሀማሴን የተባለው ቡድንም በውድድሩ ከቀድሞው አሸናፊ ግሩፖ ስፖርቲቮ አስመራ ጋር በተመሳሳይ ነጥብ የሁለተኛ ደረጃን ይዞ ለማጠናቀቅ በቃ፡፡ እጅግ ወሳኝ ተጫዋቻቸው አብርሃ ግዛው ነበር ፡፡ ሉቺያኖ ለባጎዚ በሰጠው ቃለ-ምልልስ አብርሃን " ከትውልዱ የላቀና እውነተኛ አሸናፊ! " ሲል ይገልፀዋል፡፡ አብርሃ ጥሩ የቅጣት ምት ባለሟል እንደነበር ይነገራል፡፡ ኤርትራዊ ሆኖ የጣልያን ክለብን መለያ የለበሰ የመጀመሪያው ተጫዋች ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ መባቻ የአብርሃ የፊዮረንቲና ዝውውር ጫፍ ደርሶ በዘረኝነት ችግር እንዳልተፈፀመ በጊዜው በምስራቅ አፍሪካ ከነበሩ ጣሊያናውያን የስፖርት ጋዜጠኞች መካከል ታዋቂው ኤንሪኮ ማንዴ እ.ኤ.አ በ1952 አካባቢ በወጣው መጽሔት ላይ ባሰፈረው ጽሁፉ ያስረዳል፡፡

ከኢትዮ-ኤርትራ የእግርኳስ ሊግ ውህደት በኋላ በነበሩት ሰባት ዓመታት ከኤርትራ የመጡ ቡድኖች አራት ጊዜ ሻምፒዮን መሆን ችለዋል፡፡ ሐማሴን እ.ኤ.አ በ1955 እና በ1957 ሻምፒዮናውን ሲያሸንፍ፣ አካለ ጉዛይ በ1958 እና የቴሌኮሙኒኬሽን ስፖርት ክለብ (ኋላ ገጀረት ተብሎ የተጠራው) በ1959 የሻምፒዮንነት ክብርን ተጎናጽፈዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አባላት ከኢትዮ-ኤርትራ ውህደት የተገኙ ተጫዋቾች ነበሩ፡፡

ከእነዚህ ተጫዋቾች አንዱ ሉቺያኖ ቫሳሎ ነበር። ሉቺያኖ እ.ኤ.አ በ1956 የመጀመሪያ የብሄራዊ ቡድን ጥሪ ደረሰው፡፡ ከዚያ በኋላ ከአስር ዓመታት በላይ ቁልፍ ተጫዋች ሆኖ ኢትዮጵያን አገልግሏል፡፡ ሉቺያኖ ለብሄራዊ ቡድን ከተመረጠ በኋላ የተለያዩ ተግዳሮቶች ገጥመውታል፡፡ በጊዜው ኤርትራውያኑ ተጫዋቾች በኢትዮጵያውያኑ ላይ የነበራቸው ቅራኔ የህብረት ግንኙነቱን ቀላል አላደረገውም፡፡ ሉቺያኖ እንዲያውም ከታላቁ ኢትዮጵያዊ የእግርኳስ ሰው አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ጋር የነበረው ግንኙነት መጀመሪያ ላይ ጥሩ የሚባል አልነበረም።

ሉቺያኖ በግሩፖ ስፖርቲቮ አስመራ ለሁለት ዓመታት ከተጫወተ በኋላ ወደ ድሬዳዋው ጥጥ ማህበር (ኮተን) አመራ፡፡ የወቅቱ የኢትዮጵያ ሻምፒዮን የነበሩት ኮተኖች ቡድናቸውን ለማጠናከር በሐማሴን ጥሩ አጥቂነቱን ያስመሰከረው የሉቺያኖ ታናሽ ወንድም ኢታሎን ጨምረው አስፈረሙ፡፡

በኮተን የሉቺያኖ የመጀመሪያ የውድድር ዘመን የተሳካ አልነበረም፡፡ ቡድኑ በከተማ ተቀናቃኙ ኢትዮ ሲመንት ከባድ ፉክክር ገጥሞት የዋንጫ ድሉን ማስጠበቅ ሳይችል ቀረ፡፡ እ.ኤ.አ ከ1960-1965 ድረስ ሁለቱ የምስራቅ ኢትዮጵያ ኃያላን በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ላይ ከፍተኛ የበላይነት አሳይተዋል፡፡ ኮተን ክለብም በቫሳሎ ወንድማማቾች ብቃት ታግዞ ሶስት የሊግ ድሎችን እ.ኤ.አ በ1962፣ በ1963 እና በ1965 ተጎናፀፈ፡፡ ቡድኑ በአፍሪካ የአሸናፊዎች – አሸናፊ ዋንጫ ግማሽ ፍጻሜ መድረስ ችሎ ነበር።

በ3ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የቫሳሎ ወንድማማቾች የብቃት ከፍታ በገሀድ ታየ፡፡ የፍጻሜው ጨዋታ እ.ኤ.አ በጥር 1962 በአዲስ አበባ ስታዲየም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመልካችነት የተደረገ ነበር፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት እ.ኤ.አ በ1960 አበበ ቢቂላ በሮም ኦሎምፒክ በባዶ እግሩ ሮጦ ባመጣው ተዓምራዊ የወርቅ ሜዳልያ ድል የአገሪቱን የስፖርት ግርማ ሞገስ ከፍ አድርጎት ነበር፡፡ በእርግጥ በ1960ው የአፍሪካ ዋንጫ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውጤት አስከፊ የሚባል ነበር፡፡ በሶስት ቡድኖች ተሳትፎ ብቻ በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ኢትዮጵያ በተባበሩት አረብ ሪፐብሊክ (ግብጽ) እና ሱዳን 5 ጎሎች ተቆጥረውባት፤ ምንም ጎል ሳታስቆጥር ከውድድሩ ተሰናበተች፡፡

ይህ ደካማ ውጤት አቶ ይድነቃቸው ተሰማን አነቃቸው፡፡ በኤርትራውያን ተጫዋቾች ላይ የነበራቸውን ቸልተኝነኝትም እንዲተው አደረጋቸው። የቡድኑ ድክመት አቶ ይድነቃቸው ቀድሞ በብሔራዊ ቡድኑ የሚታየውና ኤርትራውያንን ያለማካተት ልማድን እንዲለውጡ አስገድዷቸው በቡድኑ ውስጥ ከስድስት በላይ ቋሚ ተሰላፊ ኤርትራውያን ታዩ፡፡ አቶ ይድነቃቸው የአምበልነት ማዕረጉን ለሉቺያኖ ለመስጠት ባይፈልጉም በቡድን አጋሩ መንግስቱ ወርቁ ጉትጎታ ሉቺያኖ በአምበልነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን እንዲመራ ተደረገ፡፡

በአራት ቡድኖች መካከል በተካሄደውና በ3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስታዲየም በተደረገው የመጀመሪያ የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታ በሉቺያኖ 2 ጎሎች፣ በመንግስቱ 1 ጎል እና በተክሌ ኪዳኔ ተጨማሪ 1 ጎል አማካኝነት ኢትዮጵያ ቱኒዝያን 4-2 ረታች፡፡

በፍፃሜው ጨዋታ ግብጾች ባልተረጋጋው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ላይ በ35ኛው ደቂቃ በበደዊ አብድልፈታህ አማካኝነት ጎል አግብተው እስከ 75ኛው ደቂቃ ድረስ በመሪነት ዘለቁ፡፡ በ75ኛው ደቂቃ ላይ ተክሌ ኪዳኔ ኢትዮጵያን አቻ አደረገ፡፡ የበደዊ ሁለተኛ ግብ ግብፅን ዳግም መሪ አደረገ፡፡ ጨዋታው ሊጠናቀቅ 6 ደቂቃዎች ሲቀሩ ሉቺያኖ ያስቆጠራት ግብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን ወደ ዳግም አቻነት መለሰች፡፡ ይህች ጎል የግብጾችን ሞራል አወረደች። በጭማሪው ሰዓት ኢትዮጵያውያኖች በተዳከሙት ግብጾች ላይ ከፍተኛ ብልጫን አሳዩ፡፡ ኢታሎና መንግሥቱ አከታትለው ጎሎችን በማስቆጠር ለብሔራዊ ቡድናቸው የ 4 ለ 2 ድልን አስገኙ፡፡ ኢትዮጵያም የአፍሪካን ዋንጫ አሸነፈች፡፡

በእግርኳስ ሕይወት የመጨረሻ ዓመታት የቅዱስጊዮርጊስ ስፖርት ክለብን በአሰልጣኝነት ጭምር ያገለገሉት የኢትዮጵያ እግርኳስ ባለውለታ ሉቺያኖ ቫሳሎ ኑሮአቸውን ባደረጉበት ጣሊያን ሀገር በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በመስከረም 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። እኛም እኝህን የኢትዮጵያ እግርኳስ ባለውለታ ነፍስ ይማር ለማለት እንወዳለን።

# ስፖርት





## የፕሪሚየር ሊጉ የዲሲፕሊን ጉዳይ ወዴት እያመራ ነው?

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ እግር ካስ ከሚታሙበት ነገሮች አንዱ የሥነ ምግባር (ዲሲፕሊን) ጉዳይ ዋነኛው ነው፡፡ ከሀገሪቱ ትልቁ የውድድር እርከን ፕሪሚየር ሊግ አንስቶ እስከታችኛው ድረስ ከስፖርቱ ሥነምግባር ያፈነገጡ ብዙ ነገሮች ይታያሉ፣ ይሰማሉ፡፡

በእግር ካሱ በተለይም ትልቅ በሚባለው ፕሪሚየር ሊግ ትልልቅ የዲሲፕሊን ችግሮች መፈጠራቸው አዲስ ነገር ባይሆንም፣ ሀገርን በትልልቅ መድረኮች የሚወክሉ ተጫዋቾች በሚመረጡበት ሊግ ላይ ዛሬም ድረስ መቀጠላቸው ግን ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም፡፡ በተለይም ሊጉ የዲ ኤስ ቲቪ ቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ሽፋን እያገኘና ብዙ መሻሻሎች እየታዩበት በሚገኝበት በዚህ ወቅት የሥነምግባር ጉዳይ ትኩረት አለማግኘቱ አስገራሚ ነው፡፡

በተደጋጋሚ ከዲሲፕሊን ግድፈት ጋር በተያያዘ ችግሮችን ሲፈጥሩ የሚስተዋሉት ተጫዋቾች ብቻ አይደሉም፣ ለተጫዋቾች አርዓያ መሆን የሚገባቸው አሠልጣኞችና የቡድን መሪዎች ጭምር ዋና ተዋናይ ሆነው የሚታዩባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም። የዲሲፕሊን ጉዳይ በፕሪሚየር ሊጉ ምን ያህል አሳሳቢ እየሆነ እንደመጣ የሊግ ካምፓኒው በዘንድሮው የውድድር ዓመት የመጀመሪያ ዙር ከቅጣት ያገኘው ገቢ መመልከት በቂ ማሳያ ነው፡፡

ሊግ ካምፓኒው በመጀመሪያው ዙር 837 ሺ ብር የቅጣት ገቢ መሰብሰቡን በቅርቡ ባደረገው ግምገማ ማሳወቁ ይታወሳል፡፡ ከፍተኛ የቅጣት ገቢ በማስገባት አንደኛ ደረጃን የያዘው የኢትዮጵያ ቡና እግር ኳስ ክለብ ሲሆን፣ ከተከታዩ አዳማ ከተማ በእጥፍ የሚበልጥ ሲሆን ያስገባው ገቢም 259,500 ብር ሆኗል።




በሊጉ እስካሁን ምንም አይነት የገንዘብ ቅጣት ያልተቀጣው ብቸኛው ክለብ ፋሲል ከነማ ነው። ከጥፋት አይነቶች ከፍተኛ ገቢ በማምጣት "መሳደብ" የአንበሳውን ድርሻ ሲወስድ 569 ሺ ብር ማስገኘት ችሏል።

በአንድ ጨዋታ ላይ ከአንድ ቡድን "ከ3 በላይ ተጫዋቾች ካርድ በማየት" በሚለው የጥፋት አይነትም እስከ 120 ሺ ብር ቀላል የማይባል ገቢ ማስገባት ተችሏል። በተጨማሪም በመሳደብ ብቻ አወዳዳሪው አካል ከሊጉ ክለቦች 569 ሺ ብር ማግኘት ችሏል፡፡

ይህ የዲሲፕሊን ጉዳይ በሁለተኛው ዙር ፕሪሚየር ሊግም እየባሰበት እንጂ እየተሻሻለ እንደማይገኝ በ17ኛ ሳምንት ጨዋታዎች የተላለፉ የዲሲፕሊን ውሳኔዎች ማሳያ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ውድድር አመራርና ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ መጋቢት 2 ቀን 2016 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በ17ኛ ሳምንት የተደረጉ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎችን ከዳኞች እና ከታዛቢዎች የቀረቡለትን የዲሲፕሊን ሪፖርት ከመረመረ በኋላ ያሳለፋው ውሳኔዎች ትናንት ይፋ ተደርገዋል፡፡

በሳምንቱ መርሐ ግብር በተደረጉ ጨዋታዎች አምስቱ በመሸናነፍ ቀሪ ሦስቱ በአቻ ውጤት ሲጠናቀቁ 16 ጎሎች በ13 ተጫዋቾች መቆጠራቸውን ያስታወሰው ሪፖርት፣ 46 ቢጫ ካርድ ለተጫዋቾችና ቡድን አመራሮች ሲሰጥ ሦስት ቀይ ካርድ መመዝገቡን ጠቁሟል፡፡ በሳምንቱ በአምስት ተጫዋቾች እና አንድ አሠልጣኝ ላይ የዲሲፕሊን ውሳኔ መተላለፋም ታውቋል፡፡ አቤል አሰበ (ድሬዳዋ ከተማ) ሁለተኛ ቢጫ ካርድ የሚያሰጥ ጥፋት በመፈፀሙ በቀይ ካርድ ከጨዋታ ሜዳ የተወገደ ሲሆን አንድ ጨዋታ እንዲታገድ ተደርጓል፡፡ አድናን ረሻድ(አዳማ ከተማ) እና ቢንያም ፍቅሩ(ወላይታ ዲቻ) የተጋጣሚን ተጫዋች በመማታት በቀይ ካርድ ከጨዋታ ሜዳ የተወገዱ ሲሆን ለፈፀሙት ጥፋት በኢትዮጵያ እግር ካስ ፌዴሬሽን የዲሲፕሊን መመሪያ መሠረት አራት ጨዋታ እንዲታገዱና በተጨማሪ የሦስት ሺ ብር ቅጣት እንዲከፍሉ ተወስኗል። አስቻለው ታመነ(መቻል) እና ያሬድ ካሳዬ(ኢትዮጵያ መድን) በተለያዩ አምስት ጨዋታዎች የቢጫ ካርድ ማስጠንቀቂያ የተመለከቱ ሲሆን ተጫዋቾቹ ለፈፀሙት ጥፋት አንድ ጨዋታ እንዲታገዱና በተጨማሪ 1500 ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍሉ እንዲሁም አሠልጣኝ ገብረክርስቶስ ቢራራ/መቻል/ ክለቡ ከከባሕር ዳር ከተማ ጋር በነበረው ጨዋታ በተጋጣሚ ቡድን አሠልጣኝ ላይ ለፀብ የሚያነሳሳ የሥነምግባር ድርጊት ስለመፈፀማቸው ሪፖርት ቀርቦ አሠልጣኙ አራት ጨዋታ እንዲታገዱና በተጨማሪም አምስት ሺ ብር እንዲከፍሉ ተወስኗል።

በሦስት ክለቦች ላይም የዲሲፕሊን ውሳኔ ተላልፏል። ከወልቂጤ ከተማ ተጫዋቾች ሄኖክ ኢሳያስ፣ ጌቱ ኃ/ማርያም፣ ዳንኤል ደምሴ፣ አዳነ በላይነህ እና መሳይ ጳውሎስ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተጫዋቾች በረከት ግዛው፣ ዮናስ ለገሰ፣ ሐብታሙ ሸዋለም፣ ሱሌማን ሀሚድ እና ኪቲካ ጅማ እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ ሔኖክ አንጃው፣ አቤል አሰበ፣ ሄኖክ ሐሰን እና መሐመድ አብዱላጢፍ በተለያዩ ጥፋቶች ካርድ የተሰጣቸው በመሆኑ ሦስቱ ክለቦች በመመሪያው መሠረት አምስት ሺ ብር እንዲከፍሉ ሲወሰን በተጨማሪም ድሬዳዋ ከተማ በሳምንቱ ጨዋታ የክለቡ ደጋፊዎች ድንጋይ ወደ ሜዳ ስለመወርወራቸው ሪፖርት ቀርቦ ክለቡ ሃያ አምስት ሺ ብር እንዲከፍል ተወስኗል።